# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

**አዘጋጆች፡-**

ዘላለም መለሰ

ዝናሽ ሰለሞን

እንዬ ጀንበሬ

**አርታኢ፡-**

ዓይን አዲስ አንተነህ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች፡-**

እንግዳ ዘውዴ(ዶ/ር)

አወቀ ጸጋዬ

**የማጣሪያ ንባብ፡-** ኢሳያስ ይልማ

*የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ*

መግቢያ......vi
ምዕራፍ አንድ......2
የሀገር ፍቅር......2
ትምህርት አንድ፡- ስለሀገር ፍቅር የቀረበን ምንባብ አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ......3
ትምህርት ሁለት፡- ሰዕሎችን ተመልክቶ መናገር......4
ትምህርት ሦስት፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ መዘመር......5
ትምህርት አራት፡- አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ማስረዳት......5
ትምህርት አምስት ፡- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት......10
ትምህርት ስድስት፡- ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ......13
ምዕራፍ ሁለት......14
ኮቪድ 19......14
ትምህርት አንድ፡- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ የተጓደሉ ቦታዎችን ማሟላት......15
ትምህርት ሁለት፡- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ......19
ትምህርት ሦስት፡- ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን መናገር......19
ትምህርት አራት፡- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት......24
ትምህርት አምስት፡- ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል......24
ምዕራፍ ሦስት......28
የአየር ንብረት......28
ትምህርት አንድ፡-አዳምጠው የተረዱትን መናገር......29
ትምህርት ሁለት፡- የድምጽ ጥብቀትን አዳምጦ መለየት......30
ትምህርት ሦስት፡- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ማቅረብ......31
ትምህርት አራት፡- የንባብ ስልቶችን መለየት......32
ትምህርት አምስት፡- ግጥምን አንብቦ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት......35
ትምህርት ስድስት፡- ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መገልገል......38
ትምህርት ሰባት፡- የቃል ክፍሎችን መለየት......40
ምዕራፍ አራት......43
ሥርዓተ ፆታ......43
ትምህርት አንድ፡- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን መናገር......44

ትምህርት ሁለት፡- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረብ ................................ 45
ትምህርት ሦስት፡- ቃላትን ለመረዳት ማንበብ ............................................................ 46
ትምህርት አራት፡- አጣማሪዎችን(አያያዦችን) በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም .................. 49
ትምህርት አምስት፡- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት................................................... 51
ትምህርት ስድስት፡- ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም ......... 53
ምዕራፍ አምስት ................................................................................................ 55
ኑ ግብር እንክፈል .............................................................................................. 55
ትምህርት አንድ፡- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ መለየት................. 56
ትምህርት ሁለት፡- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጦ ምላሽ መስጠት... 57
ትምህርት ሦስት ፡- በምልልሶች በንቃት መሳተፍ ........................................................ 57
ትምህርት አራት፡- የምንባብን ይዘት መተንተን............................................................ 57
ትምህርት አምስት፡- አንቀጽ መጻፍ ......................................................................... 60
ትምህርት ስድስት፡-ቃላትን በትክክል መጥራት ........................................................... 62
ምዕራፍ ስድስት................................................................................................... 65
ሳይንስና ቴክኖሎጂ................................................................................................ 65
ትምህርት አንድ፡- ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ................ 66
ትምህርት ሁለት፡- አዳምጠው የተረዱትን መናገር ....................................................... 67
ትምህርት ሦስት፡- በሚና ጨዋታ መሳተፍ.................................................................. 68
ትምህርት አራት፡- በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብቦ መግለጽ .................................. 69
ትምህርት አምስት፡- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሁፎችን አንብቦ ይዘታቸውን መተንተን.......... 71
ትምህርት ስድስት፡- የጽሕፈት ደረጃዎችን መዘርዘር ..................................................... 74
ትምህርት ሰባት፡- ግጥም ማንበብ .......................................................................... 76
ምዕራፍ ሰባት ...................................................................................................... 79
ልዩ ፍላጎት .......................................................................................................... 79
ትምህርት አንድ፡- ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላት ................................ 80
ትምህርት ሁለት፡- በሚና ጫወታ መሳተፍ................................................................... 82
ትምህርት ሦስት፡- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ አስተያየት መስጠት .. 83
ትምህርት አራት ፡- አንቀጽ መጻፍ ........................................................................... 85

- ትምህርት አምስት ፡- የማመልከቻ ደብዳቤ ..... 85
ምዕራፍ ስምንት ..... 89
- ሱስና መዘዙ ..... 89
- ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር መናገር ..... 90
- ትምህርት ሁለት፡ -ብማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ማጠቃለልና ታሪክ መናገር ..... 91
- ትምህርት ሦስት፡- የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ ..... 92
- ትምህርት አራት፡- አንብቦ መረዳት ..... 94
- ትምህርት አምስት፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ ..... 96
- ትምህርት ስድስት፡- ምሳሌያዊ ንግግሮች ..... 99
ምዕራፍ ዘጠኝ ..... 101
- ሀገር በቀል ዕውቀቶች ..... 101
- ትምህርት አንድ፡- ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት ልምድ መለዋወጥ ..... 102
- ትምህርት ሁለት፡- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገር ..... 103
- ትምህርት ሦስት፡- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ መናገር ..... 106
- ትምህርት አራት፡- ድርሰት መጻፍ ..... 107
- ትምህርት አምስት፡- የተረቶችን ዋና ሀሳብ መናገር ..... 109
- ትምህርት ስድስት፡- አፈ ታሪኮችን መናገር ..... 111
- ምዕራፍ አስር ..... 114
አጭር ልቦለድ ..... 114
- ትምህርት አንድ ፡- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጦ መለየት ..... 115
- ትምህርት ሁለት፡-አጫጭር ልቦለዶችን ማንበብ ..... 118
- ትምህርት ሦስት፡- የልቦለድ አላባውያንን መለየት ..... 119
ማጣቀሻ ጽሑፎች ..... 126

# መግቢያ

ይህ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ መጽሐፉ ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት አድርጎ የተሰናዳ ሲሆን፣ ግቡም የመርሃ ትምህርቱን ዐብይና ንዑስ ዓላማዎች ከውጤት ማድረስ ነው፡፡

መማሪያ መጽሐፉ አስር ምዕራፎች አሉት፡፡ በስራቸውም በየምዕራፉ ይዘት ላይ የተመሰረቱ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች እንዲሁም የሰዋስው ዕውቀትን ለማዳበር የሚያስችሉ ተገቢ ምንባቦች ተካተውበታል፡፡ ምንባቦቹ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎችና የሰዋስው ዕውቀት ከማዳበር በተጨማሪ፣ አእምሮአቸውን የማሰልጠንና አስተሳሰባቸውን የማበልጸግ ፋይዳቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ምንባቦቹ ከዚህም አልፎ ተማሪዎች ባህላቸውን እንዲረዱ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ እውነታዎች ጋር እንዲተዋወቁ ዕድል የሚሰጡ ናቸው፡፡ የዚህ ጠቅላላ ግቡ ደግሞ ተማሪዎች በይዘቱ አማካይነት የመናገርና የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎቻቸውንና የሰውስው ዕውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ነው፡፡

በየትምህርቱ የሚመጡ ተግባራትና መልመጃዎች ከተማሪዎች ሕይወት ጋር እንዲዛመዱ የተደረጉና የችግር ፈቺነት መንፈስን የሚያነሳሱ እና አሳታፊ ናቸው፡፡ ተግባራቱም ተማሪዎች በቋንቋው በተለያዩ አቋራጭ መንገዶች እንዲገለገሉበት እድል ይሰጣል፡፡

በአጠቃላይ የመማሪያ መጽሐፉ ተማሪዎቹ የቋንቋን ክሂሎችን እንዲያዳብሩ፣ የቃላት ዕውቀታቸውን እንዲያጎለብቱና የሰውስው ችሎታቸውን እንዲያበለጽጉ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ምንባቦቹ፣ ተግባራቱና መልመጃዎቹ የተማሪዎችን አእምሮ የማበልጸግና የአስተሳሰብ አድማሳቸውን የማስፋት

እንዲሁም የችግር ፈቺነት አቅማቸውን የማጎልበት ፋይዳም አላቸው። ይህ እንዲሆን ግን የመምህራኑን ልዩ ትኩረት ይጠይቃል። በመሆኑም መምህራን መርሃ ትምህርቱን፣የመማሪያ መጽሐፉንና የመምህር መምሪያውን አዋህደው መጠቀም ይገባቸዋል።

# የአንደኛው ወሰነ-ትምህርት

# ምዕራፍ አንድ

# የሀገር ፍቅር

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስለሀገር ፍቅር ያዳመጣችሁትን ትናገራላችሁ፤
- ስዕሎችን ተመልክታችሁ መልዕክታቸውን ትናገራላችሁ፤
- አንብባችሁ የጽሑፉን ይዘት ታስረዳላችሁ፤
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ጅምር ሀሳቦችን አጠናቃችሁ ትጽፋላችሁ፡፡

## ሀ ማዳመጥ

## ትምህርት አንድ፡- ስለሀገር ፍቅር የቀረበውን ምንባብ አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ

### ተግባር

ከዚህ በማስከተል መምህራችሁ "ሀገር መውደድ ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው" በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ጽሑፉን ከማዳመጣችሁ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች፡-**
  1. ታማኝነት ጥቅሙ ምንድን ነው?
  2. ለህዝብ ታማኝ መሆን በምን ይገለጻል?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ እያዳመጣችሁ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሟችሁ በማስታወሻችሁ ያዙና ንባቡ ሲጠናቀቅ መምህራችሁን ጠይቁ፡፡

- **ድህረ ማዳመጥ**

**መልመጃ**

1. ሀገር መውደድ ማለት ሰውን መውደድ ማለት ነው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. ሀገርን መውደድ ትውልዱ ባለበት ዘመን ሀገር ምን እንደምትፈልግ ማወቅን ይጠይቃል ሲባል ምን ማለት ነው?
3. ሀገርን የመውደድ ስሜት ባለማወቅ ከተመሩ አደገኛ ውጤት ይኖረዋል የሚባለው ለምንድን ነው? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበትና ምላሻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ለ መናገር

### ተግባር

### ትምህርት ሁለት፡- ስዕሎችን ተመልክቶ መናገር






**ተግባር**

ከላይ የተመለከታችኋቸውን ስዕሎች መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ከላይ ከቀረቡ አራት ስዕሎች ምን እንደተረዳችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስዕሎቹ ከሀገር ፍቅር ስሜት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ በቡድን ተወያዩ፡፡
3. የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
4. የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ቀለማትን ትርጉም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት ሦስት፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ መዘመር

**ተግባር**

1. መምህራችሁ በጥቁር ሰሌዳ ላይ የሚጽፉላችሁን የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥም እያነበባችሁ መዝሙሩን በጋራ ዘምሩ፡፡
2. ስለ መዝሙሩ ግጥም መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩና ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### ትምህርት አራት፡- አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ማስረዳት

ቀጥሎ የቀረበው ጽሑፍ በግል የምታነቡት ነው፡፡ ምባቡን ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተሉት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

**ተግባር 1**

- **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. የሀገር ፍቅር ምንድን ነው?
2. ሀገርን መውደድ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ይመስላችኋል? ለምን?

## የሀገር ፍቅርን በምን…?

የሀገር ፍቅር ሀገርንና ህዝብን ሊጠቅሙ የሚችሉ ስራዎችን በመስራት ይገለጻል፡፡ ሰዎች በሀገር ፍቅር ስሜት በመነሳሳት የሀገራቸውን ሰላምና ደህንነት ይጠብቃሉ፤ከጠላት ይከላከላሉ፤የሀገራቸውን ሀብትና ንብረት ይንከባከባሉ፡፡ ታሪካቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ የበጎ አድራጎት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ በተጨማሪ የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ሰዎች የሰዎችን መብት ያከብራሉ፡፡ ድህነትንና ኋላቀርነት ለማስወገድ ጠንክረው ይሰራሉ፡፡ ለሰንደቅ አላማና ለብሔራዊ መዝሙር ክብር ይሰጣሉ፡፡

### ❖ ስለ ሀገር ፍቅር እስካሁን ካነበባችሁት ምን ተረዳችሁ?

የሀገር ፍቅር ስሜት የሀገርን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅና ከወራሪ ጠላት በመከላከል ይገለጻል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኞች የሀገራቸውን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅና ከወራሪ ሀይል ለመከላከል መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ የጣልያንን ወራሪ ሀይል በአድዋ፣ የሶማሊያን ወራሪ ሀይል ደግሞ በካራማራ ድባቅ መተዋል፡፡ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀውን የጠላት ሀይል በሀገር ፍቅር ስሜት ተዋግተው በማሸነፍ ማርከውታል፡፡

### ❖ ቀጥሎ ምን የምታነቡ ይመስላችኋል?

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የህዝባቸውን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ኢትዮጵያ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች ተፈቃቅረው የሚኖሩባት ሀገር መሆኗን ይረዳሉ፡፡ ህዝቦች የየራሳቸው አኗኗር፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ሀይማኖት ቋንቋና ባህል

እንዳላቸው ይገነዘባሉ። የመተሳሰብና የመረዳዳት ጠቀሜታ አውቀው ለሰላም ይታገላሉ። ተባብሮ የመኖር ባህል እንዲዳብር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ሰዎች ጠንካራ ሰራተኞች በመሆናቸው ድህነትንና ኋላቀርነትን በማሸነፍ እድገትና ብልጽግና እንዲመጣ ይጥራሉ። የተማሩት ያልተማሩ ዜጎችን ያስተምራሉ። አርሶአደሮች ከሆኑ ከፍተኛ ምርት በማምረት ሀገራቸውን ያሳድጋሉ፤ ነጋዴዎች ከሆኑ በሚያገኙት ገቢ ልክ መክፈል የሚገባቸውን ግብር ይከፍላሉ። የስራ ሀላፊዎች ከሆኑ ህዝባቸውን በቅንነት ያገለግላሉ።

ለሀገራቸው ፍቅር ያላቸው ሰዎች የበጎ አድራጎት ተግባራትን ያከናውናሉ። በራሳቸው ተነሳሽነት ለህዝባቸው አገልግሎት ይሰጣሉ። የተራቆቱ አካባቢዎችን በደን ይሸፍናሉ፤ለተጎዱ ወገኖች ደም ይለግሳሉ፤ወላጅ ያጡ ህጻናትን ያሳድጋሉ፤ጧሪ የሌላቸውን አረጋዊያን ይንከባከባሉ።

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የህዝቦች የጋራ መገልገያ የሆኑ ድልድዮችንና ተቋማትን እንደ አይናቸው ብሌን ይጠብቃሉ። አላግባብ እንዳይበላሹ በሌባ እንዳይሰረቁ በጥንቃቄ በመጠበቅ ዜጎች በጋራ እንዲጠቀሙበት ያደርጋሉ።

የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ሰዎች ሰንደቅ አላማ የአንድ ሀገር ህዝብ ሉዓላዊነትና ነጻነት የሚያሳይ ምልክት በመሆኑ ያከብሩታል። እንደ ሰንደቅ አላማ ሁሉ ለብሔራዊ መዝሙርም ትልቅ ክብር ይሰጣሉ።

(የኤፌዴሪ ት.ሚ።2003። ስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት።ገጽ ከ48-57 መነሻነት የተቀናበረ)

### ❖ ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**ተግባር**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡**

1. በኢትዮጵያ ከጣልያንና ከሶማሊያ ጋር የነበረው ጦርነት በማን አሸናፊነት ተጠናቀቀ?
2. የህዝቦችን ማንነት በመገንዘብ ተከባብሮ የመኖር ባህል መዳበር ጥቅሙ ምንድን ነው?
3. በትውልድ ውስጥ የሀገር ፍቅር ስሜት አለመኖር የሚያስከትለውን ጉዳት በቡድን ተወያዩና ሀሳባችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች ተናገሩ፡፡
4. የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲኖር ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም መልዕክቱን ለመረዳት አንብቡ፡፡

**ሀገር ማለት የኔ ልጅ**

ሀገር ማለት ልጄ፣ሀገር ማለት፣

እንዳይመስልሽ የተወለድሽበት ቦታ፣የተወለድሽበት አፈር፣

እትብትሽ የተቀበረበት፣ቀድመሽ የተነፈሽው አየር፣

ብቻ እንዳይመስልሽ፡፡

ሀገር ማለት ልጄ፣

ተፈጥሮ ከቸረችው በረከት፣ የላቡን ፍሬ የሚበላ፣

ሀገር ማለት ወገን ነው፣ የኔ የምትይው ከለላ፡፡

ትመኪበት ጥሪት፣ትደምቂበት ብርሃን፣

የስዕብናሽ ግማሽ ውል፣ ወገን ነው ማህተምሽ፡፡

ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ፡፡

መሬትማ የኔ ልጅ፣

በእምነትና ዕውቀትሽ፣ ከልለሽ ካላበጀሽው፣

ለእድገትሽ ውጥን ካልሆነ፣ለተስፋሽ ካልተመገብሽው፣

መሬትማ ባዳ ነው፣ ላለማው የሚለማ፣

ለተስማማው የሚስማማ፣

ጅረቱማ ግድ የለውም፣ቦይ ለማሰለት ይፈሳል፡፡

መሬቱ አይደለም የኔ ልጅ፣እድርተኛው ነው ሀገርሽ፣

ስትቸገሪ ታድጎ፣ስትታመሚ አስታሞ፣ስትሞቺ አፈር የሚያለብስሽ፣

በእጅሽ ያለ ብሩህ ተስፋ፣ ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ፣

ወገን ነው ልጄ ሀገርሽ፡፡

(በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)፣1999፡፡ ለማስተማሪያነት ተቀንጭቦ የተወሰደ)

## ተግባር

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግጥሙን መሰረት በማድረግ መልሱ፡፡**

1. የግጥሙን ርዕስ ስትመለከቱ ማን ለማን የጻፈው ይመስላችኋል?
2. በግጥሙ መሰረት ሀገር ማለት ምንድን ነው?
3. የግጥሙን መልዕክት በአጭሩ ተናገሩ፡፡

## መ ቃላት

### ትምህርት አምስት ፡- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ለተሰመረባቸው ቃላት እንደ አገባባቸው ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

**የሰላም ዋጋው ስንት ነው?**

ለመሆኑ ለሰላም ዋጋ **ተምነን** እናውቅ ይሆን? የሰላም **እጦት** የሚያስከፍለውን ዋጋስ? ሰላም ሲጠፋ ሰዎች በአካባቢያቸው ተረጋግተው መኖር ስለማይችሉ ይሰደዳሉ፤መሰረተ ልማቶች ስለሚፈርሱ ሀገር ወደ ፊት ከማደግ ይልቅ የፈረሰውን መልሶ በመጠገን ላይ **ትጠመዳለች**፤ ሀገርን በተሻለ መንገድ ለማሳደግ ይጠቅም የነበረ ሀብት **ውድመትን** ለማካካስ ይውላል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ በስደት ላይ ያሉ ሰዎች አካላዊ ጉዳት፣ ስነ ልቦናዊ ስብራት ይደርስባቸዋል፡፡ ሰላም ሰፍኖ ወደ ነበሩበት ለመመለስ እንኳን ጊዜ ስለሚወስድ ከእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሄደው ከመማር **ይገታሉ**፤ ነጋዴዎች ንግዳቸውን ከማካሄድ ገበሬዎችም ከእርሻ ሥራቸው **ይስተጓጎላሉ**፤ በየተቋማቱ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ሥራቸውን ማካሄድ አይችሉም፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢው የነበረው ሰላማዊ ሕይወት ይመሰቃቀላል፤ኑሮው **ይቃወሳል**፤ የሀገር ኢኮኖሚም ይወድቃል፡፡

ለመሆኑ የሰላም አለመኖር ሀገር እንደሚያፈርስ አስበን እናውቅ ይሆን? በአለማችን ብዙ ሀገራት በዚህ ምክንያት የከፈሉትን ዋጋስ? ኢራቅ፣ የመን፣ሊቢያ፣ ሶሪያ ሰላም በማጣት የፈረሱ ሀገራት ናቸው፡፡ በነዚህ ሀገራት

በአንድ ወቅት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በሀገራቸው ሰላማዊ አየር እየተነፈሱ ሕይወታቸውን የሚመሩ ነበሩ፡፡

የመኖች በሰላም እጦት ከሀገራቸው ተሰደው ኢትዮጵያ ድረስ መጥተዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ሀገራቸው ሰላም እያለ የሚበሉት የሚጠጡት በቤታቸው ሞልቶ ተርፎ ነበር፡፡ አሁንስ ? አሁንማ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች መንገድ ዳር ከልጆቻቸው ጋር ቁጭ ብለው የእለት **ጉርስ** ይለምናሉ፡፡

እኛስ የሰላምን ዋጋ እንዴት ነው ማሰብ ያለብን? ሰርቶ ለመብላት፣ ወጥቶ ለመግባት፣ትምህርት ቤት ሄዶ ለመማር ፣ ታሞ ለመታከም፣ ነግዶ ለማትረፍ አርሶ ምርት ለመሰብሰብ እና ከቤተሰብ ጋር በአንድነት የእለት ኑሮን ለመምራት ሰላም ዋጋው በጣም ትልቅ አይመስላችሁም?

እኛ ወጣቶች ለሰላም **እንቅፋት** የሆኑ ነገሮችን እንዴት ነው መፍታት ያለብን? ከአባቶቻችን እንደወረስነው **በሰከነ መንፈስ**፣ በምክንያታዊ አስተሳሰብ አንድ ላይ ቁጭ ብለን በመወያየት አይመስላችሁም? ባለመግባባት **ግጭት** ሲፈጠር ውጤቱን ማሰብ ተገቢ አይመስላችሁም? በቀላሉ ተወያይተን ልንፈታው የምንችለው ጉዳይ ቤተሰባችንን **እንዲበትን**፣ ንብረታችንን አውድሞ መኖሪያ በማሳጣት ለስደት እንዲዳርገን መፍቀድ አለብን? እኔ ግን አይመስለኝም፡፡ ችግር ቢኖር እንኳን ያለንበትን ዘመን በሚመጥን **በሳል አስተሳሰብ** ነገሮች የሚያደርሱትን ጥፋት ቀድመን በማሰብ ብልህነታችንን ማሳየት ይኖርብናል፡፡ እናንተስ?

(ምንጭ፡- ከአዘጋጆች)

## ተግባር

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡**

| ቃላት | የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ታማኝነት | ቃልን መጠበቅ፣ አለማጭበርበር፣ አለመስረቅ |
| 1. አርበኝነት | |
| 2. መከባበር | |
| 3. መስዋዕትነት | |
| 4. በጎነት | |
| 5. መለገስ | |
| 6. ሉአላዊነት | |
| 7. ብልጽግና | |

**ማስታወሻ**

የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ፍፁም የሆነ የትርጉም አንድነት ማለት አይደለም፡፡ የቃላት ፍቺ አንጻራዊ ሲሆን በተለያየ ዐውድ ለቃሉ የሚሰጡ ፍቺዎች ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ እሳት የሚለውን ቃል በሚከተሉት ሁለት ዐረፍተ ነገሮች እንመልከት

ሀ. ኑሮ እሳት ሆነ፡፡

ለ. ቤቱን እሳት አቃጠለው፡፡

በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር እሳት የሚለው ቃል የዋጋውን ውድነት በሁለተኛው ደግሞ ነገሮችን አቃጥሎ ወደ አመድነት የሚቀየረውን እሳት የሚገልጽ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## ሠ መጻፍ

### ትምህርት ስድስት፡- ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ

**ተግባር**

1. **ከዚህ በታች የቀረቡትን በጅምር የቀሩ ሀሳቦች ከራሳችሁ አሟልታችሁ ጻፏቸው፡፡**

ሀ. ሰንደቅ አላማ የአንድ ሀገር______________________________________________፡፡

ለ. የመንግስትና የህዝብ ሀብትን መንከባከብ_____________________________፡፡

ሐ. ጠንክሮ በመስራት ድህነትንና ኋላ ቀርነትን__________________________፡፡

መ. የተራቆቱ አካባቢዎችን በደን መሸፈን______________________________፡፡

ሠ. የኢትዮጵያ አርበኞች ሀገራቸውን ከወራሪ ለመከላከል______________፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ኮቪድ 19

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ታሟላላችሁ፤
- ስለወቅታዊ ጉዳይ አዳምጣችሁ ክርክርና ምልልስ ታደርጋላችሁ ፤
- ስለ ኮቪድ-19 አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፤
- ኮቪድ-19ኙን በተመለከተ የግል ተሞክሮዎቻችሁን ትናገራላችሁ፤
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ምዕላዶችን ታጣምራላችሁ፤ትነጥላላችሁ፤
- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡


## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ የተጓደሉ ቦታዎችን ማሟላት

### ተግባር 1

ከዚህ በማስከተል መምህራችሁ “የዳንኞ ስጋት” በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ጽሑፉን ከማዳመጣችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረበውን ስዕል ተመልከቱና የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡










### ❖ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች፡-

1. በስዕሉ የተገለጹት መልዕክቶች ምን ተብለው ይጠራሉ?

2. ስዕሉን በማየት መምህራችሁ ስለምን ሊያስደምጧችሁ እንደሆነ የገመታችሁትን ተናገሩ?

### ❖ በማዳመጥ ጊዜ

**ተግባር 2**

ቀጥሎ መምህሩ የሚያነቡላችሁ ጽሑፍ በየመሀሉ የተጓደሉ ሀሳቦች ያሉበት ነው፡፡ መምህራችሁ ጽሑፉን ሲያነቡላችሁ የተጓደለውን ሀሳብ በጽሑፍ አሟሉ፡፡

## የዳንቾ ስጋት

ወይዘሮ ዳንቾ በጌዴኦ ዞን ቡሌ በምትባል የገጠር ከተማ የምትኖር መምህርት ናት፡፡ በትርፍ ሰዓቷም በቤቷ ውስጥ ምግብ እያዘጋጀች በመሸጥ ኑሮዋን የምትደጉም ታታሪ እናት ናት፡፡ በሰሞኑን ግን አንድ አእምሮዋን እያስጨነቀ ሰላም የነሳት ጉዳይ ______________ ሲነገር በተደጋጋሚ እየሰማች ነው -የኮሮና በሽታ፡፡ የስራዋ ጸባይ የበለጠ ለበሽታው ተጋላጭ እንደሚያደርጋት ተረድታለች፡፡ ግን_____________ከሚባለው በሽታ ለመጠበቅ በትክክል ምን ማድረግ እንዳለባት አላወቀችም፡፡ ድንገት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ዱሪቲ ትዝ አለቻት፡፡ ጊዜ ሳታባክን ዱሪቲን ለማናገር ከቤቷ ስትወጣ ዱሪቲ _______________ ለመስራት ስትጓዝ አገኘቻትና ደስ አላት፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ዳንቾ ለምን እንደፈለገቻት በመግለጽ ጥያቄዋን ጀመረች፡፡

ዳንኞ፡ እባክሽ ኮሮና ስለሚባለው በሽታ ንገሪኝ እስቲ፡፡

ዱሪቲ የኮሮና ቫይረስ በሽታ ከቀላል እስከ ከባድ _______________ሕመም የሚያስከትል በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ የሚመጣው ____________ ነው፡፡ በሽታው እንደ ጉንፋን ዓይነት ቀላል ምልክቶችን አሳይቶ በራሱ ሊድን ወይም ሊባባስና እንደሳንባ ምች ፣ ከባድ የመተንፈሻ አካላት ሕመም ብሎም የኩላሊት ስራን_____________ ሞትን ሊያስከትል የሚችልና በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የሚገኝ በሽታ ነው፡፡

ዳንኞ፡ ወይ ጉድ ይገርማል አንቺዬ፣ ቆይ በምንድነው የሚተላለፈው?

ዱሪቲ፡ መተላለፊያ መንገዶቹ የተለያዩ ናቸው፡፡ በበሽታው የታመሙ ሰዎች በሚያስነጥሱበትና በሚያስሉበት ጊዜ ከታማሚው ሰው ከትንፋሽ ጋር የሚወጡ እርጥበት አዘል _______________ወደ ጤነኛው ሰው አፍና አፍንጫ ሲገቡ፣ ከታማሚው ሰው ጋር ንክኪ ሲደረግ ለምሳሌ እጅ በመጨባበጥ፣ ንጽሕናው ባልተጠበቀ እጅ ዓይን፣ አፍንጫና አፍን መነካካት፣ ያልበሰሉ የእንስሳት እና የዓሳ ምግቦችን በመመገብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ዳንኞ፡ ገባኝ፣ ግን በበሽታው የተያዘውን ሰው እንዴት እናውቃለን?

ዱሪቲ፡ የበሽታው ምልክቶች፣ ትኩሳት፣ ማሳል፣ የትንፋሽ ማጠር፣የጉሮሮ መከርከር፣ ለመተንፈስ መቸገር ናቸው፡፡

ዳንኞ፡ በጣም ከበድ ይመስላል፡፡ እሺ እንዴት መከላከል ይቻላል?

ዱሪቲ፡ መከላከያዎቹ በቀላሉ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እጅ አለመጨባበጥ፣ አለመሳሳምና አለመተቃቀፍ፣ እጅን በሳሙናና በውሃ ቶሎ ቶሎ በደንብ መታጠብ፤ እጅን በአግባቡ በሳሙናና በውሃ ሳይታጠቡ ____________________________ አለመነካካት፣ በበሽታው የታመመ ሰው ካለ አለመጨባበጥ ወይም የቅርብ ንክኪ አለማድረግ እና

ቢያንስ ______________________እርምጃ ያህል መራቅ፣ህዝብ በብዛት በተሰበሰበበት አካባቢ አለመገኘት፣ በሚያስነጥሱበትና በሚያስሉ ጊዜ አፍና አፍንጫን በታጠፈ ክንድ መሸፈን፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት ክዳን ባለው ዕቃ በአግባቡ ማስወገድ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ዳንኛ፡** ግን ድንገት በበሽታው የተያዘ ሰው ቢኖር ምንድን ነው መደረግ ያለበት?

**ዱሪቲ፡** ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ በበሽታው የተያዘ ሰው ቢያገጥም ቶሎ ወደ ህክምና ጣቢያ መሄድ እና ለሌሎች ሰዎች በሽታውን እንዳያስተላልፍ ደግሞ እራሱን ________________ ከ10-15 ቀን አንድ ክፍል ውስጥ ለብቻው መቆየት አለበት፡፡

**ዳንኛ፡** አመሰግናለሁ ዱሪቲ፣ በጣም ጥሩ ትምህርት ነው የሰጠሽኝ፡፡ የነገርሽኝን ሁሉ በማድረግ ___________________ከዚህ አስከፊ በሽታ እጠብቃለሁ፡፡ ደህና ዋይ ዱሪቲ፡፡

**ዱሪቲ፡** ደህና ዋይ ዳንኛ፤ ስለጠየቅሽኝ ደስ ብሎኛል፡፡ ለቤተሰቦችሽና ለጎረቤቶችሽም ይህንኑ ንገሪያቸው፡፡

❖ **የድህረ ማዳመጥ ተግባር**

## ተግባር 3

በሚከተሉት ጥያቄዎች መሰረት በምልልስ ተግባራት ተሳተፉ፡፡

1. አዳምጣችሁ ያሟላችሁትን በምልልስ የቀረበ ጽሑፍ እንደ ዳንኛ እና ዱሪቲ ሆናችሁ ጽሑፉን እያያችሁ ምልልሱን ደጋግማችሁ ተለማመዱ፡፡

## ለ መናገር

### ትምህርት ሁለት፡- በምንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ

በመምህራችሁ መሪነት አምስት አባላት ያሉዋቸው ሁለት ቡድኖች አዋቅሩ፡፡ በመቀጠል የኮቪድ19 በሽታ ከጉንፋን በሽታ ጋር **"ተመሳሳይ ነው"** እና "**ተመሳሳይ አይደለም**" በሚል ሀሳብ ክርክር አድርጉ፡፡ ሌሎቻችሁ በሁለቱ ቡድኖች የቀረበውን ሀሳብ በመቃወም ወይም በመደገፍ አስተያየት ስጡ፡፡

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት ሦስት፡- ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን መናገር

**ተግባር**

ከዚህ ቀጥሎ "ድንገተኛው አለም አቀፍ ወረርሽኝ" በሚል ርዕስ አንድ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ጽሑፉን ከማንበባችሁ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን አንብቡና በቃል መልሱ፡፡

❖ **የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ድንገተኛው አለም አቀፍ ወረርሽኝ የተባለው ምንድን ነው?
2. ወረርሽኝ የሚለው ቃል ምን አይነት በሽታን ይገልጻል?

❖ **በንባብ ጊዜ**

## ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ እያነበባችሁ በመሀል የሚያጋጥማችሁን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

### ድንገተኛው አለም አቀፍ ወረርሽኝ

ኢንፍሉዌንዛ፣ ጉንፋን እና ኮቪድ-19 መነሻቸው የተለያዩ ቫይረሶች ቢሆኑም፤ ምልክቶቻቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንዳቸውን ከሌላቸው ለመለየት ያስቸግራል፡፡ በኮሮና ቫይረስ የሚያዙ ሰዎች ከሚያሳዩአቸው ምልክቶች መካከል ሙቀት መጨመር፣ የማያቋርጥ ሳል፣ የስሜት ህዋሳት አልሰራ ማለት ይጠቀሳሉ፡፡ የሰውነት ሙቀት ከ37.8 በላይ ሲጨምር ሰውነት ኮሮና ቫይረስን ወይም ሌላ ህመም እየተዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ ትኩሳት የኮሮና ቫይረስ ብቻ ሳይሆን የጉንፋንና የሌሎች ህመሞችም ምልክት ነው፡፡ ኮቪድ-19፣ ኢንፍሉዌንዛ ወይም ጉንፋን ሲይዝዎ ያስልዎታል፡፡

ጉንፋን ድንገት ይከሰትና የጡንቻ ህመም፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ራስ ምታት፣ የጉሮሮ መድረቅ፣ድካም፣ የአፍንጫ መታፈን ያስከትላል፡፡ ህመሙ ከኢንፍሉዌንዛ በላይ ነው፡፡ ኢንፍሉዌንዛ የሚሰማን ቀስ በቀስ ሲሆን፤ ህመሙም ቀለል ይላል፡፡ ሳል፣ ማስነጠስ፣ የጉሮሮ መድረቅ እና የአፍንጫ ፈሳሽ ምልክቶቹ ናቸው፡፡ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ የጡንቻ ህመምና ራስ ምታት ላይገጥም ይችላል፡፡

ኮሮና ቫይረስ ሲይዝ በ24 ሰዓት ውስጥ ሁለቴ ወይም ሦስቴ ከአንድ ሰዓት በላይ የማያቋርጥ ሳል ያስከትላል፡፡ መቅመስና ማሽተት ካቃተዎ ወይም ጣዕም መለየት ካልቻሉ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ማድረግ አለብዎት፡፡ አልፎም ሰውነት ማሳከክ፣

ድካም፣ ጉሮሮ ማሳከክ እና የራስ ምታት ሊያጋጠምዎ ይችላል። ሳል መጀመሪያ ሲጀመር ደረቅ ያለ ነው። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ አክታ የተቀላቀለበት ይሆናል። እነዚህን ምልክቶች በቂ እረፍት በማድረግ፣ ፈሳሽ በመጠጣትና በፓራሲታሞል ክኒን ማከም ይቻላል። በሌላ በኩል ማስነጠስ የኮሮና ቫይረስ ምልክት አይደለም።

❖ ቀደም ሲል ካነበባችኋቸው አንቀጾች ኮቪድ 19 በሽታን ከሌሎቹ የሚለየው ምንድነው?

በተጨማሪም የአፍንጫ ፈሳሽ የኮሮና ቫይረስ ምልክት እንዳልሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ኮቪድ-19 ያለባቸው ሰዎች መጠነኛ ወይም የተባባሰ ምልክት ሊያሳዩ ይችላሉ። ምልክት የማያሳዩ ሰዎች በሽታውን ሊያስተላልፉ ይችላሉ። በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች በሁለት ሳምንት ውስጥ ምልክቱን ያሳያሉ። በእርግጥ ብዙሀኑ በአምስተኛው ቀን የበሽታው ምልክት ሊታይባቸው ይችላል። ትንፋሽ የሚያጥርዎ ከሆነ በሽታው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። በአጠቃላይ አንዳች የኮቪድ-19 ምልክት ሰውነትዎ ላይ ካስተዋሉ ሳያንገራግሩ ወደ ህክምና መስጫ ይሂዱ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኮቪድ ተይዞ መዳን ድጋሚ ላለመያዝ ዋስትና አይሆንም። በበሽታው ታሞ የዳነ ሰው ከሦስት ወራት በኋላ እንደ አዲስ ተጋላጭ ይሆናል። ድጋሚ የሚከሰቱ ህመሞች እድሜ እና ፆታ አይመርጡም። እንደመጀመሪያው ጊዜ እስከ ሞት ድረስ የማድረስ እድል አላቸው። የኮቪድ-19 ህመም በከፍተኛ ሁኔታ የሚተላለፈው ታማሚው በቫይረሱ ከተጠቃ በኋላ ባሉት የመጀመርያዎቹ አምስት ቀናት ነው። ኮቪድ-19 የያዛቸው በርካታ ሰዎች መካከለኛ የህመም ስሜት ያሳያሉ። በጣም ልብ ልንለው የሚገባው ነገር በጣም ጥቂት ሰዎች ለብዙ ሰዎች በበሽታ መያዝ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው።

ስለዚህ ባላወቅነው አጋጣሚ የበሽታው ሰለባ እዳንሆን ሳንዘናጋ ጥንቃቄያችንን መቀጠል ይኖርብናል፡፡

(ምንጭ፡- ከጤና ሚኒስተር ድረ ገጽ ለማስተማር እንዲመች ሆኖ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. ኮቪድ-19፣ ኢንፍሉዌንዛና ጉንፋን ምልክታቸው ተመሳሳይ ቢመስልም በተለያዩ ቫይረሶች የሚመጡ በሽታዎች ናቸው፡፡

ለ. ትኩሳት በጉንፋንና በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች የሚያሳዩት የበሽታ ምልክት ነው፡፡

ሐ. ኢንፍሎዌንዛ ጉንፋን እና ኮቪድ 19 ሦስቱም በቫይረስ የሚመጡ በሽታዎች ናቸው ፡፡

መ. መቅመስና ማሽተት አለመቻል የኮሮና ቫይረስ ምልክቶች ናቸው፡፡

ሠ. አንድ ጊዜ በኮሮና ቫይረስ የተያዘ ሰው ድጋሚ በበሽታው አይያዝም፡፡

## መልመጃ ሁለት

**ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት መካከል የኮሮና ቫይረስ ምልክት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ትኩሳት ለ. ራስ ምታት ሐ. የጉሮሮ ማሳከክ መ.ሁሉም መልስ ይሆናል

2. ከሚከተሉት ስለ ኮሮና ቫይረስ ትክክል **ያልሆነው** የትኛው ነው?

   ሀ. በኮሮና የተያዙ ሰዎች ምልክት ሳያሳዩ በሽታውን ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

   ለ. የትንፋሽ ማጠር የበሽታውን ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ ያሳያል።

   ሐ. በበሽታው የታመመ ሰው ከአንድ ወር በኋላ ድጋሚ ሊያዝ ይችላል።

   መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

3. ኮሮና ቫይረስ፤ ኢንፍሉዌንዛ እና ጉንፋን የሚያመሳስላቸው ምልክት ምንድን ነው?

   ሀ. የሰውነት ማሳከክ ለ. ማስነጠስ ሐ. የአፍንጫ ፈሳሽ መ. ሳል

## መልመጃ ሦስት

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥቄዎች ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሃሳብ መነሻ በማድረግ መልሱ።**

1. በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች ኮቪድ 19 በሽታን ለመከላከል ጥንቃቄዎችን ያደርጋሉ?
2. ኮሮናን ለመከላከል ሁሉም ሰው ምን ማድረግ ይገባዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## መ ቃላት

### ትምህርት አራት፡- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ቀደም ሲል በትምህርት ሦስት የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

| ቃል | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|
| ሀ. ትኩሳት | | |
| ለ. መከሰት | | |
| ሐ. ተባባሰ | | |
| መ. ማስተዋል | | |
| ሠ. ተጋላጭ | | |
| ረ. መዘናጋት | | |
| ሰ. ህመም | | |
| ሸ. ሰለባ | | |

## ሠ ሰዋስው

### ትምህርት አምስት፡- ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል

**ተግባር**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ምዕላዶች ነጥላችሁ አስቀምጡ፡፡**

1. ቤቶች
2. ወንድሜ
3. ደብተሩ

**ማስታወሻ**

ምዕላድ ሊከፋፈል የማይችል ትርጉም ያለው አነስተኛ የቋንቋ አሀድ/ክፍል/ ነው። ምዕላዶች ነጻ እና ጥገኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ነጻ ምዕላዶች እራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ሲሆኑ ጥገኛ ምዕላዶች ደግሞ በነጻ ምዕላዶች ላይ ካልተቀጠሉ በስተቀር ለብቻቸው መቆም የማይችሉ ናቸው። ለምሳሌ ቤቶች በሚለው ቃል ውስጥ ቤት ነጻ ምዕላድ ሲሆን -ኦች ደግሞ ጥገኛ ምዕላድ ይባላል።

## ተግባር

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ውስብስብ ቃላት በምሳሌው መሰረት በምዕላድ ከፋፍላችሁ አስቀምጡ።

| ቃል | ነጻ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- ዛፎች | ዛፍ | -ኦች |
| ሀ. ቫይረሶች | | |
| ለ. ምልክቶች | | |
| ሐ. ሴቶች | | |
| መ. ስሜቶች | | |
| ሠ . በሬዎች | | |

2. ቀጥሎ የተሰጡትን ምዕላዶች በማቀናጀት ቃላትን መስርቱ፡፡

| ምዕላዶች | | |
|---|---|---|
| ነጻ ምዕላድ | ቅጥያዎች | ቃል |
| ምሳሌ፡- ሰለባ | -ዎች | ሰለባዎች |
| ልብስ | -ኤ | |
| ተጋላጭ | -ኦች | |
| ፈተና | -ሀ | |
| ምግብ | -ኣችን | |
| ደረቅ | -ኦች | |

## ትምህርት ስድስት፡- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት

**ማስታወሻ**

ዐረፍተ ነገር የተሟላ ሀሳብ የሚይዝ፣ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ልናስተላልፍ የፈለግነውን ሀሳብ የምንለዋወጥበት የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡ ዐረፍተ ነገሮች በሰዋስዋዊ ቅርጻቸው ነጠላ ወይም ድርብ ሆነው ሊዋቀሩ ይችላሉ፡፡ ነጠላ ዐረፍተ ነገር አንድ ባለቤትና አንድ ማሰሪያ አንቀጽ ያለው ሲሆን ድርብ ዐረፍተ ነገር ደግሞ ከአንድ በላይ ነጠላ ዐረፍተ ነገሮች በአያያዥ ቃላት ወይም በድርብ ሰረዝ ተያይዘው የሚገኙበት ነው፡፡

## ተግባር

**1. ቀጥሎ የተሰጡትን ዐረፍተ ነገሮች ነጠላ ወይም ድርብ ዐረፍ ተነገር በማለት ለዩ።**

ሀ. ሰውዬው ትላንት መጣ።

ለ. ደመናው ከብዷል፤ ዝናብ ሳይጥል አይቀርም።

ሐ. ስብሰባው ተበተነ።

መ. ጀሚላ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነች።

ሠ. ፍለጋው ቀጥሏል፤ ይሁን እንጂ ወንጀለኛው እስካሁን አልተያዘም።

2. ስለ ነጠላና ድርብ ዐረፍተነገር አመሰራረት በተማራችሁት መሰረት አራት ነጠላ ዐረፍተ ነገሮችንና አራት ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቱና ለመምህራችሁ አሳዩ።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአየር ንብረት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፤
- የድምጽ ጥብቀትን አዳምጣችሁ ትለያላችሁ፤
- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፤
- በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን ትጠቀማላችሁ፤
- የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ትለያላችሁ፤
- ግጥም አንብባችሁ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- የቃል ክፍሎችን ትለያላችሁ።

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡-አዳምጠው የተረዱትን መናገር

**ተግባር**

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የአየር ንብረት ለውጥ ምንድን ነው?
2. በምድር ላይ የሙቀት መጨመር ምን ችግር ያስከትላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

የአየር ንብረት ለውጥ የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝ በንቃት አዳምጡ፡፡ በመምህራችሁ ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

- **ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት መልሱ፡፡**

1. ከምድር ጋር ያለንን ግንኙነት ልናሻሽል የምንችለው ምን ስናደርግ ነው?
2. ሙቀት በከፍተኛ ሁኔታ ሲጨምር የሚከሰተውን ጉዳት ግለጹ፡፡
3. የምድር ሙቀትን ለመቀነስ መፍትሔው ምንድን ነው?

## ትምህርት ሁለት፡- የድምጽ ጥብቀትን አዳምጦ መለየት

**ተግባር**

**የሚከተለውን አንቀጽ መምህሩ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾችን ትርጉም ለዩ፡፡**

__በሬ__ ላይ ቁጭ ብዬ __በሰባ__ ብር የገዛሁትን ጫማ እግሬ ላይ ስሞክር __ለገና__ በዓል የተገዛው __የሰባ__ __በሬ__ __ገና__ በወንድሞቼ እየተጎተተ ወደ ግቢያችን መግባቱ ነበር፡፡ ከኋላዬ ቁጭ ብላ __እንስራ__ ስታጥብ የነበረችው የልጄ __አያት፣__ እረ ኑ! የበዓል ሥራ __እንስራ__ እንጂ! ስትል ተጣራች፡፡ ልጄም የአያቱን ድምጽ ድንገት ሲሰማ ደንገጥ ብሎ ዞር ብሎ __አያት__፡፡

**ምሳሌ፡-**

በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ ያለው __በሬ__ የሚለው ቃል ጠብቆ የሚነበብ ሲሆን ደጃፍ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡

በሁለተኛው መስመር ያለው __በሬ__ ደግሞ ላልቶ የሚነበብ ሲሆን እንስሳውን ይጠቁማል፡፡

**ማስታወሻ**

የድምጽ ጥብቀት ማለት በቃል ውስጥ የሚገኙ ድምጾች ጫን ወይም ረገጥ ተደርጎ መጠራት ማለት ነው፡፡ ድምጾች ጠብቀውና ላልተው በመነበባቸው ምክንያት የትርጉም ለውጥ ያመጣሉ፡፡

## ለ መናገር

### ትምህርት ሦስት፡- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ማቅረብ

<u>**ማስታወሻ**</u>

**በንግግር አቀራረብ ወቅት የሚከተሉትን መመሪያዎች ተከተሉ።**

- የንግግሩን ርዕስና ዓላማ በአጭሩ አስተዋውቁ።
- ንግግሩን በሙሉ ልብ አቅርቡ።
- የድምጽ ቃናና የአካል እንቅስቃሴያችሁን ማራኪ አድርጉ።
- ስትናገሩ የተደራሲያንን ስሜት ጠብቁ።
- ታዳሚዎች እየተከታተሉዋችሁ መሆኑን በዓይናችሁ ቃኙ።
- በመጨረሻም የተደራሲያንን ጥያቄና አስተያየት ተቀበሉ።

### ተግባር

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ችግር በሚመለከት አንድ ርዕስ ምረጡ። ቀጥሎም በመረጣችሁት ርዕስ ላይ በቡድን ተወያዩ። የተስማማችሁበትን ሀሳብ በአግባቡ አደራጁ። ከዚያም ከቡድናችሁ አንድ ሰው ወክሉና ከላይ በቀረበው የንግግር አቀራረብ መመሪያ መሰረት ለክፍል ተማሪዎች ንግግር አቅርቡ።

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት አራት፡- የንባብ ስልቶችን መለየት

**ማስታወሻ**

የንባብ ስልቶች እንደምናነብበት ዓላማና እንደ ጽሑፉ ዓይነት የተለያዩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ለተለያየ ዓላማ የምንጠቀምባቸውን የንባብ ስልቶችን እንመለከታለን፡፡

1. **የአሰሳ ንባብ፡-** ይህ የንባብ ስልት ዓላማው ቀደም ብለን የምናውቀውን ከፊል መረጃ በአእምሮአችን ይዘን ቀሪውን ለማሟላት የምናካሂደው ነው፡፡ ስልቱም የሚፈለገው ጉዳይ እስኪገኝ ዓይንን ከግራ ወደቀኝ በፍጥነት በማንቀሳቀስ ይከናወናል፡፡ ለምሳሌ፡- የቦታ (የድርጅት) ስሞች፣ ስልክ ቁጥር፣ የትውልድ ቦታ፣ ዓ/ምህረት ወዘተ. ፈልጎ ለማግኘት የሚደረግ ንባብ፡፡

2. **የገረፍታ ንባብ፡-** የዚህ የንባብ ስልት ዓላማው ከሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ ቀልብን የሚስብ ወይም ከፍላጎትና ከዝንባሌ ጋር የተያያዘ ቁምነገር ምናልባት ባገኝበት በሚል በፍጥነት በሚደረግ ቅኝት የሚከናወን ነው፡፡

   ለምሳሌ፡- ከጋዜጣ ወይም ከመጽሄት ቀልብን የሚስብ ነገር በፍጥነት በዐይን መቃኘት ይጠቀሳል፡፡

3. **ጥልቅ ንባብ፡-** ይህ የንባብ ስልት አእምሮን ለማዳበር፣አመለካከትን ለማስፋትና ዕውቀትን ለማደርጀት ታስቦ በማስተዋል የሚደረግ የጥናት ንባብ ነው፡፡

   ለምሳሌ፡- ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር የተያያዙ ጽሑፎችን በጥልቀት ማንበብ ይጠቀሳል፡፡

4. **ሰፊ ንባብ፡-** ለጠቅላላ ዕውቀትና ለመዝናናት የሚደረግ የንባብ ስልት ነው፡፡

   ለምሳሌ፡- ልቦለዶችንና የተለያዩ መጣጥፎችን ማንበብ ይጠቀሳል፡፡

❖ **ቅድመ ንባብ ጥያቄ**

1. ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮችን ዘርዝሩ፡፡

## የአየር ንብረት

የአየር ንብረት ማለት በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የአየር ሙቀት ፣የዝናብ መጠን፣ የአየር እርጥበት፣ የነፋስ ፍጥነት፣ ወዘተ.ሁኔታዎች ለመግለጽ የምንጠቀምበት አገላለጽ ነው፡፡ ይህ ለረጅም ጊዜያት የተመዘገበው ሁኔታ የአየር ንብረት ለውጥ ያስከትላል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ከሚያስከትላቸው ችግሮች መካከል የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት መቀነስ ይጠቀሳል፡፡ አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሥራ ነው፡፡ የህዝቡ ቁጥር መጨመርም ተጨማሪ የምግብ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው፡፡ይህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው፡፡ አካባቢ ላይ ጫና ሲደርስ የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ሊቀንስና ቁጥሩ እያደገ የሚገኘውን ህዝብን መመገብ አዳጋች የሚሆንበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

የኢትዮጵያ መልክአ ምድር ተራራማ፣ ኮረብታማ እንዲሁም ዝቅተኛ ቦታዎችና ሜዳዎች የሚበዛበት ነው፡፡ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶችም መነሻቸው ከደጋማው አካባቢ በመሆኑ የመሬቱ አቀማመጥ ከወንዞቹ የፍሰት አቅጣጫ ጋር ተዳምሮ ለአፈር መሸርሸር የተመቸ አድርጎታል፡፡ በዚህ ምክንያት አፈሩ እየታጠበ ወደጎረቤት ሀገር መጓዙ የተለመደ ሆኗል፡፡ ይህም የአየር ንብረት ለውጥን ከማባባሱ በተጨማሪ የድርቅ መከሰትን፣ የበረሀማነትን መስፋፋት፣የግብርና ምርት መቀነስን፣ የተፈጥሮ ሚዛን መቃወስን የመሳሰሉትን አስከትሏል፡፡ የቤትና የዱር እንስሳትም የአየር ንብረት ለውጥ በሚፈጥረው የጤና ችግር ተጠቂዎች

ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ይቀንሳሉ፡፡ የሀገር ውስጥ ፍጆታ አቅርቦትም ይቀንሳል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ችግር በዘላቂነት ለመመከት እንዲያስችላት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በመንደፍ ለውጡን ለመከላከል ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

አረንጓዴ ልማት ለህዝቧ የህልውና እና የኑሮ መሰረት በመሆኑ እየተሰራ ያለ ሥራ ደግሞ ዓለም ጭምር በሞዴልነት እየወሰደ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ይህንኑ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በማስቀጠል ረገድም ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ በስፋት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ እንደአብነት አቢይ አህመድ በመዲናችን አዲስ አበባ ያስጀመራቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፣የአካባቢ ጥበቃንና የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የተፈጥሮ ሀብትም ሆነ የእጽዋትና ደኖች የመመናመን ጉዳይ በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋትና ቀውስ ከፍተኛ መሆን ከግምት ውስጥ ያስገቡት ጠቅላይ ሚኒስቴር አቢይ አህመድ መላው የሀገራቸውን ህዝብ ከጎናቸው በማሰለፍ የአረንጓዴ ልማት አርበኛ በማድረግ ረገድ ትልቅ ስኬትን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

በሀገሪቱ ሁሉም ክፍሎች በተደረገው የችግኝ ተከላ በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ትልቅ ትኩረትን የሳበ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያሳተፈው የችግኝ ተከላ አሁንም በስፋት ቀጥሏል፡፡ ኢትዮጵያን በአፍሪካና በአለም አቀፍ መድረክ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ሞዴል የማድረግ እንቅስቃሴው የበርካታዎችን ይሁንታና ድጋፍ እያገኘ መሆኑን በስፋት እያስተዋልን ነው፡፡ በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ አረንጓዴ ውበት ይኖራት ዘንድ ችግኝ

መትከል፣ዕጽዋቶችን መንከባከብና ደኖችን ከጭፍጨፋ መከላከል የሁሉም ሰው ሀላፊነት በመሆኑ ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል፡፡

(ተረፈ ወርቁ፣ከድረ ገጽ ለማስተማር እንዲመች ተደርጎ የቀረበ)

**ተግባር**

**ሀ. ከላይ በማስታወሻ ክፍል ከቀረቡት የንባብ ስልቶች የአሰሳ የንባብ ስልትን በመጠቀም የአየር ንብረት በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ፡-**

1. የኢትዮጵያ መልክአ ምድር ዓይነቶችን ጥቀሱ፡፡
2. ሀገራችን ኢትዮጵያ አረንጓዴ ውበት ይኖራት ዘንድ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
3. ጠቅላይ ሚኒስተር አቢይ አህመድ መላው የሀገራቸው ህዝብ ከጎናቸው እንዲሰለፍ ያደረገው ተግባር ምንድነው?

**ለ. ጥልቅ የንባብ ስልትን በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ችግሮች አስረዱ፡፡
2. ኢትዮጵያን ለአፈር መሸርሸር አደጋ የተመቸች እንድትሆን ያደረጓት ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

## ትምህርት አምስት፡- ግጥምን አንብቦ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ቀጣዩን ግጥም አንብቡና በመልመጃ አንድና ሁለት ላይ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

## ሀገሬ

አገሬ ውበት ነው፤
ለምለምና ነፋስ የሚጫወትበት፣
ፀሐይ የሞላበት፣ ቀለም የሞላበት።
አገሬ ቆላ ነው፤ ደጋ ወይናደጋ
እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ።
አገሬ ተራራ፣ ሸለቆ ረባዳ፣
አገሬ ጅረት ነው ገደልና ሜዳ።
ውሸት ነው በበጋ ፀሐይ አትፋጅም፤
ክረምቱም አይበርድም፤
አይበርድም፤ አይበርድም።
አገሬ ጫካ ነው፤
እንስሳት አራዊት የሚፈነጩበት፤
በወጥመድ ሳይገቡ ሳይነካቸው ጠላት።

(ገብረክርስቶስ ደስታ፣1998፣ገጽ139፣ ለማስተማሪያነት ተቀንጭቦ የተወሰደ)

### መልመጃ አንድ

**ግጥሙን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት በተመሳሳይ ፍቻቸው አዛምዱ**

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. | ጫካ | ሀ. ከፍታ ያለው መሬት |
| 2. | ጅረት | ለ. ጎድጎድ ያለ አካባቢ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | ደጋ | ሐ. | ሞቃት አካባቢ |
| 4. | ውበት | መ. | የሙቀት ወቅት |
| 5. | ክረምት | ሠ. | በእጽዋት ያማረ አረንጓዴ አካባቢ |
| 6. | ተራራ | ረ. | ዛፎች የበዙበት ቦታ |
| 7. | በጋ | ሰ. | ማማር |
| 8. | ቆላ | ሸ. | ቀዝቃዛ አካባቢ |
| 9. | ሸለቆ | ቀ. | ወንዝ |
| 10. | ለምለም | በ. | የዝናብ ወቅት |

**መልመጃ ሁለት**

ግጥሙን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት በተቃራኒ ፍቻቸው አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ቆላ | ብርድ |
| ተራራ | በጋ |
| ገደል | ሜዳ |
| ክረምት | ረባዳ |
| ሙቀት | ደጋ |

## መ መጻፍ

## ትምህርት ስድስት፡- ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መገልገል

### ተግባር

**ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ የትኞቹ የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች እንደተካተቱ ግለጹ፡፡**

ባለፈው ሳምንት አርብ ከአንድ የገበያ አካባቢ ቆሜ ነበር፡፡ አንዲት በእድሜ ጠና ያሉ ሴት "ተጨካከን እኮ!..ተጨካከንን!" እያሉ ብቻቸውን ጮክ ብለው እየተናገሩ ወዳለሁበት አካባቢ መጡ፡፡ ነገሩ ግራ ስላጋባኝ "ምነው እማማ ምን ሆኑ?" ብዬ ጠየኳቸው፡፡ "እንዴ! ከመሬት የሚወጣ ጨው ወዴት ሄዶ ነው የሚጠፋው?" እንዴት በአንድ ጊዜ ጨው አስር ብር ይገባል? ደሃ ምን ይብላ? በርበሬ እንዳንበላ በርበሬ ተወደደ፤ቃሪያ በውሃ ነክረን እንዳንበላ ቃሪያ ተወደደ፤ አሁን ደግሞ ጨው ነስንሰን እንዳንበላ ጨው ተወደደ፡፡ ታዲያ ምን እንሁን? ጨው ብቻ እኮ አይደለም የቤት ኪራይ፣የጤፍ ዋጋ፣የትራንስፖርት ዋጋ፣የአትክልት ዋጋ፣የህክምና ዋጋ ምን ያልጨመረ ነገር አለ…?!

(ዳንኤል ክብረት፣2003፣ገጽ 93 ተቀንጭቦ የተወሰደ)

### ተግባር

**አንቀጹን ስታነቡ የለያችኋቸውን የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች ለምን አገልግሎት እንደገቡ ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡**

## ተግባር

**ቀጥለው በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አስገቡ፡፡**

1. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ማለትም እንደሳሙና ዘይት ሸቀጣሸቀጦች ጥራጥሬዎች ዋጋቸው በእጥፍ ጨምሯል
2. አካባቢው በአበቦች አጊጧል የሳሩ ልምላሜ ቀልብን ይሰውራል የህጻናቱ ቡረቃ ሀሴትን ይፈጥራል የክረምቱ ወራት መጠናቀቁ ሳይሆን አይቀርም
3. ጀግና ነው ያንን ሁሉ ፈተና አልፎ ተሸላሚ ሆነ

**ማስታወሻ**

ሥርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ የሚተላለፍ መልዕክት ሳይዛባ በትክክል እንዲቀርብ የሚያደርጉ ምልክቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሥርዓተ ነጥቦችን በጽሑፍ ውስጥ በአግባቡ መጠቀም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተወሰኑትን የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች መማራችሁ ይታወሳል፡፡ የቀደሙትን በማጠናከር በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሥርዓተ ነጥቦችን በተመለከተ የሚከተለው ማስታወሻ በማጠናከሪያነት ቀርቦላችኋል፡፡

1. **ቃለ አጋኖ** (!)፡- ከፍ ያለ ስሜትን ማለትም ደስታን፣ ብስጭትን፣ ቁጣን፣እርካታን፣ ንዴትን፣ መደነቅን፣ ወዘተ. ከሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮች፣ ሀረጎችና ቃሎች በኋላ ይገባል፡፡

   ምሳሌ፡-

   ሀ.ወይ ጉድ! ብሎ ብሎ በሕይወቴ ይምጣ!

   ለ. እሰይ! እንኳን በሰላም ተገላገለች!

2. **ነጠላ ሰረዝ(፣)**፡- ተመሳሳይ ሰዋስዋዊ ሙያ ባላቸውና ተከታትለው በሚዘረዘሩ ቃላትና ሀረጋት መካከል ይገባል፡፡

   ምሳሌ፡-

ሀ. የኢትዮጵያ መልክአ ምድር ተራራማ፣ኮረብረታማ፣ዝቅተኛ ቦታዎችና ሜዳዎች የሚበዙበት ነው፡፡

ለ. የኢትዮጵያ መልክአ ምድር የተለያየ መሆን የድርቅ መከሰትን፣ የበረሀማነት መስፋፋትን፣ የግብርና ምርት መቀነስንና የተፈጥሮ ሚዛን መቃወስን አስከትሏል፡፡

3. **ድርብ ሰረዝ( ፤ )**፡- እርስ በእርስ በሀሳብ ተደጋግፈው የሚዘረዘሩ ዐረፍተ ነገሮች መሀል ይገባል፡፡

ምሳሌ፡- የኢትዮጵያ መልክአ ምድር የተለያየ መሆን ድርቅን ያስከትላል፤ በረሀማነትን ያስፋፋል፤ የግብርና ምርት መቀነስንና የተፈጥሮ ሚዛን መቃወስን ያባብሳል፡፡

4. **ትምህርተ ጥቅስ፡-("    ")** በጽሑፍ ውስጥ ወይም በንግግር ወቅት ቀደም ሲል በሌላ ሰው የተባለን ወይም በመጽሐፍ የሰፈረ ሀሳብ እንዳለ ለመጥቀስ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- "ችግኝ በመትከል አረንጓዴ አሻራችንን እናኑር" አሉ ጠቅላይ ሚኒስተሩ

## ሠ ሰዋስው

### ትምህርት ሰባት፡- የቃል ክፍሎችን መለየት

**ማስታወሻ**

የአማርኛ የቃል ክፍሎች በአምስት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፡- ስም፣ቅጽል፣ ግስ፣ መስተዋድድና ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡ ከነዚህ የቃል ክፍሎች መካከል በዚህ የክፍል ደረጃ ሶስቱን እንመለከታለን፡፡ እነዚህም ስም፣ቅጽልና ግስ ናቸው፡፡

1. **ስም**፡- የነገሮች ስያሜ ወይም መጠሪያ ሲሆን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ወይም

ተሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ፡-

ሀ. <u>ዛፍ</u> የአካባቢን አየር ነፋሻ ያደርጋል፡፡ ዛፍ የሚለው ቃል የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነ ስም ነው፡፡

ለ. <u>ልጁ</u> <u>ችግኝ</u> ተከለ፡፡ ልጁ የሚለው ቃል የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነ ስም ሲሆን ችግኝ የሚለው ደግሞ ተሳቢ የሆነ ስም ነው፡፡ ተሳቢ በአረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት ተቀባይ ቃል ነው፡፡

2. **ቅጽል፡-** የስም ገላጭ የሆነ የቃል ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም ስሙን በዓይነት፣ በመጠንና በግብር ይገልጻል፡፡

ምሳሌ፡- **ሀ.** **<u>ጥቁሩ</u>** በሬ ሞተ፡፡ ጥቁሩ የሚለው ቅጽል የበሬውን ዓይነት የሚገልጽ ገላጭ ነው፡፡

**ለ.** **ረጅሙ** ዛፍ ተቆረጠ፡፡ ረጅሙ የሚለው ቅጽል የዛፉን ቁመት የሚገልጽ ገላጭ ነው፡፡

**ሐ.** **<u>ጎበዙ</u>** ተማሪ ተሸለመ፡፡ ጎበዙ የሚለው የተማሪውን ግብር የሚገልጽ ገላጭ ነው፡፡

3. **ግስ፡-** ድርጊት አመልካች የሆነ የቃል ክፍል ሲሆን በአረፍተ ነገር አገባብ በመጨረሻ ይገኛል፡፡

ምሳሌ፡- ተማሪው የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት **አጠናቀቀ**፡፡ አጠናቀቀ የሚለው ቃል ልጁ ያከናወነውን ድርጊት የሚናገር ግስ የሆነ ቃል ነው፡፡

## ተግባር

1. በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ስም፣ቅጽል እና ግስ የሆኑት ቃላትን በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አውጡ፡፡

| | ስም | ቅጽል | ግስ |
|---|---|---|---|

| ምሳሌ፡- አሮጌው ቤት ታደሰ፡፡ | ቤት | አሮጌው | ታደሰ |
|---|---|---|---|
| ሀ. አደገኛው ወንጀለኛ ተፈረደበት፡፡ | | | |
| ለ. ጠይሟን ልጅ እወዳታለሁ፡፡ | | | |
| ሐ. ፈጣን መኪና ያስፈልገኛል፡፡ | | | |
| መ. አጭበርባሪው ነጋዴ ከሰረ፡፡ | | | |
| ሠ. ሰፊው ጫካ ተመነጠረ፡፡ | | | |
| ረ. ሀይለኛ ጉንፋን ይዞኛል፡፡ | | | |

2. በየግላችሁ አምስት አረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ በመሰረታችሁት ዐረፍተ ነገር ውስጥ ስም፣ ቅፅል እና ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ሥርዓተ ፆታ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ሥርዓተ ጾታን የተመለከተ ምንባብ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፡፡
- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- ቃላትን ለመረዳት ጽሑፍን ታነባላችሁ፡፡
- አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ትለያላችሁ፤
- በዐረፍተ ነገር ደረጃ ስዋስዋዊ መዋቅሮችን በትክክል ትጠቀማላችሁ፡፡

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን መናገር

ከዚህ በማስከተል መምህራችሁ “መንፈሰ ጠንካራዋ አሚና” በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ከማዳመጣችሁ በፊት ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል በትኩረት ተመልከቱ፡፡ ቀጥሎም የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡



**ተግባር**

- **የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

**1. ስዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡**

- **በማዳመጥ ጊዜ**

"መንፈሰ ጠንካራዋ አሚና" በሚል የቀረበውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በንቃት በማዳመጥና ዋና ዋና ነጥቦችን በመጻፍ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

- **ድህረ ማዳመጥ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት መልሱ፡፡**

ሀ. አሚና ምን ዓይነት ሴት ናት? የደረሰባት ጥቃትስ ምንድን ነው?

ለ. አሚና የደረሰባትን ጥቃት እንዴት ተቋቁማ አለፈችው?

ሐ. አሚናን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያነሳሳት ምንድን ነው?

## ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረብ

**ተግባር**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች በምዕራፍ ሦስት ስለ ንግግር አቀራረብ የተማራችሁትን እያስታወሳችሁ ስሩ፡፡

1. ከፆታ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የእያንዳንዱ ሰው ሚና ምን መሆን አለበት? በቡድን ተወያዩና የተስማማችሁበትን ሀሳብ ከየቡድኑ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በመወከል ሀሳባችሁን ለክፍል ተማሪዎች የንግግር ሥርዓትን በመከተል አቅርቡ፡፡

2. በቡድናችሁ በመሆን በምትኖሩበት አካባቢ የአሚና ዓይነት ችግር የገጠመው ሰው ታሪክ አጠያይቃችሁ ታሪኩን በወረቀት ጽፋችሁ ተለማመዱና ከቡድናችሁ አንድ ተማሪ በመወከል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አቅርቡ።

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት ሦስት፡- ቃላትን ለመረዳት ማንበብ

**ተግባር**

- **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. በምትኖሩበት አካባቢ ማህበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
2. በአካባቢያችሁ በሴቶች ላይ ሲደርሱ የምታዩዋቸውን ማህበራዊ ጫናዎች ጥቀሱ።

- **በንባብ ጊዜ**

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ እያነበባችሁ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በአገባባቸው መሰረት ፍቺ ስጡ።

## ሥርዓተ ፆታ

ሥርዓተ ፆታ ማለት ማህበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጣቸውን ቦታ የሚወስንላቸውን **ሚና** የሚያንጸባርቀውን አመለካከት እና የሚኖረውን የወንዶችና የሴቶች ግንኙነትን፣ ወዘተ. የሚያመለክት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች **ተፈጥሮአዊ** አይደሉም። ይልቁንም ከተወለዱ በኋላ በማህበረሰባቸው ሴት ወይም ወንድ በመሆናቸው ብቻ የሚሰጣቸው ነው። ሰዎች እነዚህን አስተሳሰቦችና **ልማዶች** ከማህበረሰባቸው ይማሩታል።

ሥርዓተ ጾታ ከቦታ ቦታ እንደ ማህበረሰቡ ባህል እምነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ይለያያል። በአንድ ባህል ውስጥ እንኳን ከቦታ ቦታ ልዩነት ይኖራል። በብዙ ባህሎች ውስጥ ወንዶች ልጆች ወንድነትን **አጉልተው** በሚያሳዩ ባህሪያት **ኮትኩተው** ያድጋሉ። ሴቶችም እንዲሁ የሴትነትን ባህሪይ **እንዲላበሱ** ይደረጋል። ማንኛውም ማህበረሰብ **ሥርዓተ ፆታን** ለመግለጽ ጾታን እንደ አንድ መመዘኛ ይጠቀማል። ከዚህ አንጻር እንደአገራችን ባሉ በርካታ ማህበረሰቦች ውስጥ በወንዶችና በሴቶች መካከል ሰፊ የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች አሉ። እነዚህም በአብዛኛው ሴቶችን ከወንዶች የሚያሳንሱና የወንዶችን የበላይነት የሚያንጸባርቁ ናቸው። እነዚህ ልዩነቶች በሴቶች **ሁለንተናዊ** ህይወት ውስጥ ከፍተኛ **አሉታዊ ተጽዕኖ** ያሳድራሉ። ስለዚህ የሥርዓተ ጾታ አመለካከት **መዛባትን** አወንታዊ በሆነ መልኩ መለወጥ ያስፈልጋል።

በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን **ተጨባጭ ሁኔታ** ስንመለከት **ስናራምደው** የቆየነው የሥርዓተ ጾታ ግንኙነት ለወንዱ **ያደላ** መሆኑን እንገነዘባለን። በውጤቱ የሴቶች ቁጥር በውሳኔ ሰጪነት ቦታ፣ ኢኮኖሚን በመቆጣጠር ረገድ፣በትምህርት ተሳትፎ ወዘተ. በጣም አንሶ እንዲገኝ አድርጎታል። አሁን ባለንበት ዘመን

የማህበረሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች ሳያሳትፉ የሚፈለገውን ልማት ማምጣት አይቻልም። ስለዚህ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ከፍ ማድረግና የጾታ እኩልነትን ማሳደግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሴቶችን ከወንዶች ከሚያሳንሱና የወንዶችን የበላይነት ከሚያንጸባርቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ባሻገር በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሌሎች ተጽዕኖዎችም አሉ። ለምሳሌ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከሆኑት ግርዛት፣ያለእድሜ ጋብቻ፣ በወሊድ ጊዜና በወር አበባ ጊዜ **መገለል** ይጠቀሳሉ። ከዚህም ባሻገር ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት እንዲሁም **የውርስ ጋብቻ**፣መደፈር በመሳሰሉት ምክንያቶች ለኤች አይ ቪ እና ለሌሎች የአባላዘር በሽታዎች እንዲሁም ላልተፈለገ እርግዝና መጋለጥ ይታያል።

በሴቶችና በህጻናት ጉልበት ላይ **ጥገኛ መሆንም** ሌላው አሳሳቢ ችግር ነው። ሴት ልጆች በህብረተሰቡ ብሎም በወላጆች በሚደረግባቸው የስራ ጫናና በየደረጃው በሚገጥሟቸው ጥቃቶች በትምህርት ተሳትፏቸው እና በውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጠራል። ወላጆችም ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ሴት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ አለመቻላቸው ሁኔታውን **አስከፊ** ያደርገዋል።

ባጠቃላይ ከሥርዓተ ፆታ ልዩነት ጋር ተያይዞ **ስር የሰደደ** ልማዳዊና ባህላዊ የአመለካከት ችግር እንዳለ ይታያል። ይህን አመለካከት ለመለወጥ ተከታታይ ትምህርት በመስጠት **ኋላቀር** ከሆኑ አስተሳሰቦች ህብረተሰቡን **አላቆ** ሴቶች ከጥቃት ተጠብቀው ከወንዶች እኩል በእድገት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉበትን መንገድ ማመቻቸትና መብቶቻቸውን ማስጠበቅ የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሀላፊነት ይሆናል።

(መልካም አስተዳደርና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ከጌዲኦ ዞን ምክር ቤት ጋር በመተባበር ሚያዝያ 1999 ዓ/ም ካዘጋጀው ጽሁፍ ለማስተማሪያነት እንዲስማማ ተደርጎ የተሻሻለ)

❖ **ድህረ ንባብ ጥያቄ**

የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ።

1. በቡድን ተከፋፍላችሁ በስድስቱ አንቀጾች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት እንደአገባባቸው የያዙትን ፍቺ መሰረት በማድረግ የአንቀጾቹን መልዕክት ተወያዩበት። በመጨረሻም የተረዳችሁትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድኖች አስረዱ።

## መ መጻፍ

### ትምህርት አራት፡- አጣማሪዎችን (አያያዦችን) በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም

**ተግባር**

1. **ቀጥሎ በሰንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ ዐረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አጣማሪዎች (አያያዦች) መካከል ተገቢውን በመጠቀም የተሟላ ሀሳብ መስርቱ።**

| | ዐረፍተ ነገር | አጣማሪ (አያያዥ) | ዐረፍተ ነገር |
|---|---|---|---|
| 1. | የሥርዓተ ፆታ አመለካከት ተፈጥሮአዊ አይደለም። | ይሁን እንጂ | በማህበረሰቡ ሴት ወይም ወንድ በመሆን የሚሰጥ ነው። |
| 2. | የማህበረሰባችን አመለካከት ለወንዶች ያደላ ነው። | ይልቁንም | ለሴቶች የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል። |
| 3. | ሴቶች በወላጆቻቸው ከፍተኛ | ስለዚህ | ጫናውን ተቋቁመው ለውጤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የስራ ጫና ይደረግባቸዋል፡፡ | | የሚበቁ ሴቶች አሉ፡፡ |
| 4. | ከፆታ እኩልነት ጋር የተያያዘ የአመለካከት መዛባት አለ፡፡ | ነገር ግን | ለሴቶች የሚሰጠውን ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ |
| 5. | ሴቶች የማህበረሰቡ ግማሽ አካል ናቸው፡፡ | በመሆኑም | በሚፈለገው መጠን ትኩረት አልተሰጣቸውም፡፡ |

**2. የተለያዩ አጣማሪዎችን (አያያዦችን) በመጠቀም አምስት ዐረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

**ማስታወሻ**

አጣማሪዎች ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮችን በማያያዝ ሀሳብ ሳይቆራረጥ ትርጉም ባለው ሁኔታ እንዲገለጽ ያደርጋሉ፡፡

ምሳሌ፡ ሎምባሜ ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

በወላጆቿ ድጋፍ አይደረግላትም፡፡

ሎምባሜ ጎበዝ ተማሪ ናት፤ ይሁን እንጂ በወላጆቿ ድጋፍ አይደረግላትም፡፡

በምሳሌው መሰረት ይሁን እንጂ የሚለው አጣማሪ (አያያዥ) ሁለቱን ዐረፍተ ነገሮች በማያያዝ ሀሳቡ በአንድ ዐረፍተ ነገር ተጠቃሎ እንዲገለጽ አድርጓል፡፡

## ሠ ሰዋስው

### ትምህርት አምስት፡- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት

**ተግባር**

1. **በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሀረጉንና ግሳዊ ሀረጉን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

   ምሳሌ፡- የዘንድሮው ምርጫ / በሰላም ተጠናቀቀ፡፡

   ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

   ሀ. ጥቁሩ ጃኬት ገመዱ ላይ ተሰቅሏል፡፡

   ለ. እርጥብ እንጨት ትላንት ወደከተማ ተጫነ፡፡

   ሐ. ወጣገባ መንገድ ለመራመድ አይመችም፡፡

   መ. ኋላቀር አስተሳሰብ በትምህርት ይለወጣል፡፡

   ሠ. አስተዋይ ሰው ለነገ ያስባል፡፡

   ረ. ጨቅጫቃው ወንድሜ በቅርቡ ይመጣል፡፡

2. አንድ የስም ገላጭና አንድ የግስ ገላጭ ያላቸውን አምስት ዐረፍተ ነገሮች መስርታችሁ ስማዊ ሀረጉንና ግሳዊ ሀረጉን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

**ማስታወሻ**

ዐረፍተ ነገር የሚገነባው ከሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ነው፡፡ እነሱም ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ተብለው ይጠራሉ፡፡ ከእነዚህ መሰረታዊ የዐረፍተ ነገር ክፍሎች አንዱ ከጎደለ ዐረፍተነገሩ መኖር አይችልም፡፡ እያንዳንዳቸውን በምሳሌ እንመልከት፡፡

1. **ስማዊ ሀረግ፡-** ስማዊ ሀረግ የዐረፍ ተነገሩ ባለቤት የሆነውን ስም ብቻ ወይም ስሙንና ሌሎች የስሙን ገላጮች በመያዝ ይዋቀራል፡፡

**ምሳሌ፡-**

**ሀ.** መሬቱ ታረሰ። በዚህ ዐረፍተ ነገር መሬቱ የሚለው ስም ብቻውን ስማዊ ሀረግ ይባላል። ይህ ቃል ባይኖር የታረሰው ምን እንደሆነ ስለማይታወቅ ዐረፍተ ነገሩን ጎዶሎ ያደርገዋል።

**ለ.** ሰፊው መሬት ታረሰ። በዚህ ዐረፍተ ነገር ደግሞ ሰፊው መሬት የሚለው ስማዊ ሀረግ ይሆናል። መሬት ባለቤት የሆነው ስም ሲሆን ሰፊውየሚለው ደግሞ የመሬቱን መጠን የሚገልጽ የስም ገላጭ ነው። በዚህ ሁኔታ ስሙ ብቻውን ወይም አንድና ከዚያ በላይ ገላጮች ገልጸውት ሊመጣ ይችላል።

2. **ግሳዊ ሀረግ፡-** ግሳዊ ሀረግ ማለት ምን ሆነ ወይም ምን ተደረገ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ነው። በመሆኑም አመላካቹን ቃል መሪ አድርጎ በመያዝ ግሱ ለብቻ ወይም ከሌሎች ድርጊቱን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ፣ ወዘተ  አንጻር ከሚገልጹ ገላጮች ጋር አብሮ የሚዋቀር ነው።

**ምሳሌ፡-** **ሀ.** ጎረቤቴ ታመመ። በዚህ ዐረፍተ ነገር ግሱ ታመመ የሚለው ቃል ነው።ታመመ የሚለው ቃል በሌለበት ስሙ ብቻውን ዐረፍተ ነገር መሆን አይችልም።

**ለ.** ጎረቤቴ ክፉኛ ታመመ። በሚለው ዐረፍተ ነገር ደግሞ ታመመ ግሱ ሲሆን ክፉኛ ደግሞ የህመሙን ሁኔታ የሚያመለክት ሆናል።

ከዚህ የምንረዳው ግሱ ለብቻው ወይም ከሌሎች ገላጮች ጋር ሊዋቀር መቻሉን ነው። በዚህ ምክንያት ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ መቅረት የማይችሉ የዐረፍተ ነገር ክፍሎች ናቸው ማለት ይቻላል።

## ትምህርት ስድስት፡- ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም

### ተግባር

1. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች የሰዋስው (የመዋቅር) ስህተት ያለባቸው ናቸው፡፡ ዐረፍተ ነገሮቹን በጥንቃቄ አንብባችሁ ስህተቱን በመለየት አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ንጽህናውን የማይጠብቅ ሰው በቀላሉ ለበሽታ ሊጋለጥ ይችላሉ፡፡

ለ. ሙስጠፋና ጎረቤቶቹ ጎበዝ ገበሬዎች በመሆናቸው ቤተሰባቸውን ከችግር ማዳን ችሏል፡፡

ሐ. ወላጆች ልጆቻቸውን የመንከባከብ ሀላፊነት አለበት፡፡

መ. ሾይጫ በጣም ስለጠማው ውሃውን በአንድ ትንፋሽ ጨለጠችው፡፡

ሠ. አያንቱ ተክሎችን በጣም ሰለምትወድ ዘወትር ይንከባከባቸዋል፡፡

ረ. እነ ሻንካ ጎበዝ እስፖርተኞች ነን፡፡

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች በመመልከት በምሳሌው መሰረት የሰዋስው ችግሩ ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡

| | ምሳሌ፤- ላሚቷ ሳር በላ፡፡ | የፆታ አለመስማማት |
|---|---|---|
| ሀ. | መሰረት የሌለው ቤት ቶሎ ትፈርሳለች፡፡ | |
| ለ. | በርካታ ነጋዴዎች ትርፋቸው እንደቀነሰ ገለጻችሁ፡፡ | |
| ሐ. | የመንደራችን ሽማግሌዎች የተጣሉ ሰዎችን አስታረቀ፡፡ | |
| መ. | ሚልኪ ባሌቤቱን በጣም ያከብሯታል፡፡ | |
| ሠ. | አጎቴ ሰኞ ትመጣለች፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| ረ. | የከድር ቤተሰቦች በቅርቡ ሠርግ ለመደገስ ተዘጋጅቷል፡፡ | |
| ሰ. | እናንተ ነገ ለስራ ይፈለጋሉ፡፡ | |
| ሸ. | ሙሽራው በጣም አምሮባታል፡፡ | |

**ማስታወሻ**

ሰዋስው በዐረፍተ ነገር መዋቅር ቃላትና ሀረጋት የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቀው በአግባቡ መቀናጀታቸውን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡ ቃላትና ሀረጋት ሥርዓታቸውን ጠብቀው በአግባቡ ካልተዋቀሩ/ካልተቀናጁ በዐረፍተ ነገሩ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ሊዛባ ይችላል ፡፡ የሰዋስው መዛባት ከሚያመጡ ምክንያቶች አንዱ የዐረፍተ ነገር ባለቤትና ግሱ በመደብ፣ በፆታና በቁጥር አለመስማማት ነው፡፡

ምሳሌ፡- በመልካም ስራቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ በርካታ ሰዎች በየአካባቢያችን አለ፡፡ በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ "ሰዎች" የሚለው የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነው ቃል ሰዎቹ በቁጥር ብዙ መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን "አለ" ሚለው ግስ ግን ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም በባለቤቱና በግሱ መካከል የቁጥር አለመስማማት ችግር አለ ማለት ነው፡፡

ዐረፍተ ነገሩን አስተካክለን ስንጽፈው እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

በመልካም ስራቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ በርካታ ሰዎች በየአካባቢያችን አሉ፡፡

በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን የገለጽንበት መደብ፣ፆታና ቁጥር በግሱ ውስጥ ተመሳሳይ ሆኖ መገለጽ አለበት፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# ኑ ግብር እንክፈል

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጣችሁ ትለያላችሁ፤
- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፤
- በምልልሶች በንቃት ትሳተፋላችሁ፤
- የምንባቡን ይዘት ትተነትናላችሁ፤
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ጥሩ ተናጋሪዎች ቃላትን እንዴት በትክክል እንደሚጠሩ ትገመግማላችሁ፤

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ መለየት

**ተግባር**

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ግብር (ታክስ) መክፈል ማለት ምን ማለት ነው?
2. ግብር መክፈል ያለበት ማን ነው?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

መምህሩ የሚያስደምጣችሁን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ የጥያቄ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

- **ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ ባስደመጧችሁ ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. ምንዳ ምን አይነት ነጋዴ ነው?
2. በግብር አከፋፈል ላይ የምንዳ አቋም ምንድን ነው?
3. ታደለ በመጨረሻ የምንዳን አቋም ተቀበለ ወይስ ተቃወመ?
4. የታደለን የግብር አከፋፈል አቋም እንዲስተካከል ያደረገው ምንድን ነው?
5. እናንተም ስለግብር መክፈል አስፈላጊነት የተረዳችሁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?

## ትምህርት ሁለት፡- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጦ ምላሽ መስጠት

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያስደምጧችሁን በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎች አዳምጣችሁ ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ።

## ለ መናገር

## ትምህርት ሦስት ፡- በምልልሶች በንቃት መሳተፍ

### ተግባር

1. ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ በተከታዩ መንገድ ሚና ወስዳችሁ በንቃት በመሳተፍ ተጫወቱ።

   ሚና አንድ፡- ግብር በወቅቱ የሚከፍል ነጋዴ ሆኖ መተወን።

   ሚና ሁለት፡- ግብር በወቅቱ የማይከፍል ነጋዴ ሆኖ መተወን።

## ሐ ማንበብ

## ትምህርት አራት፡- የምንባብን ይዘት መተንተን

### ተግባር

- **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ኮንትሮባንድ ምንድን ነው?
2. የኮንትሮባንድ ንግድ ምን አይነት ጉዳት ያለው ይመስላችኋል?

## ኮንትሮባንድ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

የኮንትሮባንድ ንግድ ተገቢው ግብር የማይከፈልበት በመሆኑ የመንግስትን ገቢ ያሳጣል፡፡ ሀገራችን በየዓመቱ በርካታ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን እንደ መንገድ፣ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች የልማት ስራዎችን ለመስራት የሚስችላትን ገቢ ያሳጣል፡፡ ከዚህም ሌላ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የገበያ ተወዳዳሪነት ይቀንሳል፤ከወጪና ገቢ ንግድ የሚገኘን ግብር እና ቀረጥ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪን ያሳጣል፡፡ በሌላ መልኩ በዜጎች መካከል ሰፊ የገቢ ልዩነትን ከማስከተሉም ባሻገር በህቀኛ ግብር ከፋዮች ላይ የግብር ጫናን ከፍ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ጥቁር ገበያን በማስፋፋትና የሸቀጦችን ዋጋ በማናር የዋጋ ግሸበትን ስለሚፈጥር በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ኑሮ ያከብዳል፡፡ እንዲሁም ልማት በሚፈለገው ፍጥነትና መጠን እንዳይስፋፋ በማድረግ ድህነት በመቀነስ ፋንታ እንዲባባስ ያደርጋል፡፡

❖ **ተማሪዎች እስካሁን ባነበባችሁት መሰረት የኮንትሮባንድ ንግድ ጉዳቱ ምንድን ነው?**

ኮንትሮባንድ በአንድ ሀገር ላይ ለሚያስከተለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በተጨማሪም የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው ሃይሎች ሽብርን በመፍጠር አሉታዊ የፖለቲካ ተጽዕኖ ለማሳደር የሚያስችል አቅምን ይፈጥሩበታል፡፡ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ስጋት የሚሆኑ የዝርፊያና የግድያ ወንጀልን የሚፈጽሙ ቡድኖች እንዲፈጠሩና አቅማቸው እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በዋናነት ለመንግስት የተሰጠው ሃላፊነት

ቢሆንም ከችግሩ ስፋትና ውስብስብነት አንጻር የሁሉንም ዜጋ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድ በወንጀል የሚያስጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ህግና ደንቦችን በመተላለፍ የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች ከህጋዊ መተላለፊያ መስመሩ ውጪ በድብቅ ወደ ሀገር ካስገባ፣ ካስወጣ ወይም ከሞከረ ወይም በህገ ወጥ መንገድ ካስገባ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እንዲሁም ከብር 50ሺ እስከ 200ሺ ያስቀጣል፡፡ እንዲሁም በህገ-ወጥ መንገድ የተገኙ ዕቃዎችን ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ሰው ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50ሺ እስከ 100ሺ በሚደርስ ገንዘብ ያስቀጣል፡፡ ወንጀሉ የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ ደግሞ የእስራት ቅጣቱ እስከ 15 ዓመት ከፍ እንደሚል ህጉ ይደነግጋል፡፡

(ከገቢዎች ድረ ገጽ ለማስተማር እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

## ተግባር

- ❖ **ድህረ ንባብ ጥያቄዎች**

**ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1.የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከልና የመቆጣጠር ሀላፊነት የማን ነው?

2/ በኮንትሮባንድ ንግድ በወንጀል የሚያስጠይቁ ተግባራት ምንድን ናቸው? ዘርዝራችሁ አስረዱ፡፡

3/ ከብር 50ሺ እስከ 100ሺ በሚደርስ ገንዘብ የሚያስቀጣ የኮንትሮባድ ወንጀል ምንድን ነው?

## መ መጻፍ

## ትምህርት አምስት፡- አንቀጽ መጻፍ

### ተግባር

| |
|---|
| በአካባቢያችሁ ስለ ግብር አከፋፈል ያለውን ልምድ አጠያይቃችሁ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡ |

### አንቀጽ መጻፍ

**ማስታወሻ**

አንቀጽ አንድ ሀሳብ ብቻ የያዘ ዐረፍተ ነገሮች ቅንጅት የሚፈጠር አነስተኛ የድርሰት አካል ነው፡፡ አንድ አንቀጽ በአንድ ድርሰት ውስጥ ከሚቀርቡ የተለያዩ ሀሳቦች አንዱን ብቻ የያዘ ነው፡፡ የአንቀጹን ዋና ሀሳብ ጠቅልሎ የያዘው ዐረፍተ ነገር የአንቀጽ ኃይለ ቃል ይባላል፡፡ በኃይለ ቃሉ የተገለጸውን አቢይ ሀሳብ የሚያብራሩ ንዑሳን ዐረፍተ ነገሮች ዝርዝር ዐረፍተ ነገር ይባላሉ፡፡ አንቀጽ የተለያዩ የማስፋፊያ ስልቶች አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ምክንያትና ውጤት፣ገለጻ፣ ምሳሌ፣ ማወዳደር፣ ማነጻጸርና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የአንቀጽ ስልቶች መካከል በዚህ የክፍል ደረጃ በምክንያትና ውጤት አንቀጽ እንዴት ማስፋፋት እንዳለባችሁ ትማራላችሁ፡፡

**በምክንያትና ውጤት አንቀጽን የማስፋፋት ስልት፡-** የአንድ ነገር ውጤት ከሱ በፊት በሚኖር ምክንያት ወይም መንስኤ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚቀርብበት ነው፡፡ አንድ ምክንያት ውጤትን ሲያስገኝ በተገኘው ውጤትና ለውጤቱ መገኘት ምክንያት በሆነው ነገር መካከል ጥብቅ የሆነ ተጠየቃዊ/ምክንያታዊ ግንኙነት አለ፡፡

## ተግባር

ከላይ ኮንትሮባንድ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች በሚል ርዕስ የቀረቡትን አንቀጾች የአጻጻፍ ስልት በትኩረት ተመልከቱ፡፡ ከዚያም ቀደም ብላችሁ ስለ ግብር አከፋፈል በአካባቢያችሁ ያለውን ልምድ በተመለከተ የጻፋችሁትን ጽሑፍ የአንቀጽ አጻጻፍ ስልትን ተከትላችሁ አንደገና ጻፉት፡፡

## በምክንያትና ውጤት የተስፋፋ አንቀጽ ምሳሌ፡-

የኮንትሮባንድ መስፋፋት በአንድ ሀገር ላይ ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን እያስከተለ መጥቷል፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድ ተገቢው ግብር የማይከፈልበት በመሆኑ የመንግስትን ገቢ ያሳጣል፡፡ ሀገራችን በየዓመቱ በርካታ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን እንደ መንገድ፣ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች የልማት ስራዎችን ለመስራት የሚስያችላትን ገቢ ያሳጣል፡፡ ከዚህም ሌላ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የገበያ ተወዳዳሪነት ይቀንሳል፤ ከወጪና ገቢ ንግድ የሚገኘን ግብር እና ቀረጥ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪን ያሳጣል፡፡ በሌላ መልኩ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው ሃይሎች ሽብርን በመፍጠር አሉታዊ የፖለቲካ ተጽዕኖ ለማሳደር የኮንትሮባንድ ንግድ አቅምን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ኮንትሮባንድ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ስጋት የሚሆኑ የዝርፊያና የግድያ ወንጀልን የሚፈጽሙ ቡድኖች እንዲፈጠሩና አቅማቸው እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

**ተግባር**

ቀደም ሲል በቀረበው ምሳሌ መሰረት በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት የተስፋፋ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ሠ ቃላት

### ትምህርት ስድስት፡- ቃላትን በትክክል መጥራት

**ተግባር**

1. **ከሚከተሉት ቃላት ለመጥራት የሚያስቸግሯችሁ ድምጾች ያሉባቸውን ቃላት እየመረጣችሁ በመምህራችሁ እየታገዛችሁ በትክክል ለመጥራት ሞክሩ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ወንፊት | መ. ዘማች | ሰ. በላ |
| ለ. ወፍ | ሠ. ሽሚዝ | ሸ. ሰበረ |
| ሐ. ዛፍ | ረ. አዜመ | ቀ. በረከት |

**ማስታወሻ**

ቃላትን በትክክል መጥራት ማለት በቃሉ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በትክክለኛ አጠራራቸው (ንበታቸው) አስተካክሎ መጥራት ማለት ነው። በክልላችን አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛን ሲናገሩ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ እየገቡ የሚያስቸግሯቸው ድምጾች አሉ። እነዚህ ድምጾች እንደ የአፍ መፍቻ ቋንቋው አይነት የተለያዩ ናቸው። ለምሳሌ፡-

- በወላይትኛ አፋቸውን የፈቱ ሰዎች "ፈ" ን በፐ ቀይረው ይጠራሉ። "ፈረስ" በማለት ፈንታ "ፐረስ" ብለው ይጠራሉ።
- በኮንሶኛ አፋቸውን የፈቱ "ዘ"ን በ "ሰ" ቀይረው ይጠራሉ። "ዘመረ" በማለት ፈንታ "ሰመረ" ብለው ይጠራሉ።
- በጌዲኦኛ አፋቸውን የፈቱ "ኘ" ን በ"ነ" ቀይረው ይጠራሉ። "ሰኞ" በማለት ፈንታ "ሰኖ" ብለው ይጠራሉ።
- ሌሎች ደግሞ "እ" ን በ"ኢ" ቀይረው "እረፍት" በማለት ፈንታ "ኢረፍት" "ኧ" ን ደግሞ በ "ኤ" ቀይረው "አሰበ" በማለት ፈንታ "አሰቤ" በማለት ይጠራሉ።

ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እነዚህን የአማርኛ ድምጾች መጥራትን የሚቸገሩበት ምክንያት ድምጾቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውስጥ ባለመኖራቸው ነው። ስለዚህ እነዚህን ድምጾች ደጋግሞ መጥራት በመለማመድ ችግሩን ማስወገድ ይቻላል።

2. **ለመጥራት የሚያስቸግሯችሁን የአማርኛ ድምጾች ለይታችሁ በመምህራችሁ አጋዥነት በትክክል መጥራት ደጋግማችሁ ተለማመዱ።**

# የሁለተኛው ወሰነ-ትምህርት

# ምዕራፍ ስድስት

## ሳይንስና ቴክኖሎጂ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ምልክቶችን አይታችሁ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ታዛምዳላችሁ፤
- አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፤
- በሚና ጨዋታ ትሳተፋላችሁ፤
- በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፤
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሁፎችን አንብባችሁ ይዘቱን ትተነትናላችሁ ፤
- የጽሕፈት ደረጃዎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የግጥም አነባበብ ስልትን ተከትላችሁ ግጥም ታነባላችሁ፡፡

# ሀ ማዳመጥ

## ትምህርት አንድ፡- ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ

**ተግባር**

❖ **ቅድመ ማዳመጥ**

**መምህራችሁ ከዚህ በታች ስለምትመለከቷቸው የትራፊክ ምልክቶች ትርጉምና መልዕክት የሚያስደምጧችሁን ገለጻ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የትራፊክ መብራት ምንድን ነው?
2. የትራፊክ ምልክቶች ለምን የሚያገለግሉ ይመስላችኋል?

❖ **በማዳመጥ ጊዜ**

**ቀጥሎ መምህራችሁ የሚሰጧችሁን የትራፊክ ምልክቶች ገለጻ በስዕሉ ከቀረቡት የትራፊክ ምልክቶች ጋር አዛምዱ፡፡**

| | |
|---|---|
|  |  |
|  |  |
|  |  |

❖ **ድህረ ማዳመጥ**

**ቀጥሎ የቀረቡትን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. በስዕሎቹ ከተመለከታችኋቸው የትራፊክ ምልክቶች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. መምህራችሁ የሚያሳዩዋችሁን ተጨማሪ የትራፊክ ምልክቶች እየተመለከታችሁ ስለምልክቶቹ መምህራችሁ ከሚሰጧችሁ ቃላዊ ገለጻ ጋር አዛምዱ፡፡
3. ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ ሌሎች የትራፊክ ምልክቶችን ከመንገድ ላይ ተመልክታችሁ ወይም አጠያይቃችሁ በደብተራችሁ ስላችሁ አምጡና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- አዳምጦ መናገር

### ተግባር

**መምህራችሁ “ዓለም ሩጫ ላይ ነች እኛስ?” በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ጽሑፉን ከማዳመጣችሁ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄውን በቃል መልሱ፡፡**

❖ **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ዘመናዊ አሰራር ምንድን ነው? ጥቅሙስ?

❖ **በማዳመጥ ጊዜ**

**መምህሩ የሚያስደምጧችሁን ጽሑፍ እያዳመጣችሁ በየመሀሉ የሚጠይቋችሁን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

### ❖ ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ ባስደመጧችሁ ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ።

1. ዓለም ሩጫ ላይ ነች የተባለው ለምንድን ነው?
2. ጥንታዊ የሃገራችን ህዝቦች ሲጠቀሙባቸው የነበሩትን ጥበቦች ጥቀሱ።
3. ሀገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ኋላቀር ከሚባሉት ሀገሮች ተርታ እንድትሆን ያደረጋት ምክንያት ምንድን ነው?
4. በቴክኖሎጂ በመታገዝ አሠራርን ማዘመን፣ ማቀላጠፍና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?
5. ሀገርን በቴክኖሎጂ ለማዘመን የአዲሱ ትውልድ ሚና ምን መሆን አለበት?

## ለ መናገር

### ትምህርት ሦስት፡- በሚና ጨዋታ መሳተፍ

ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ በተከታዩ መንገድ ሚና ወስዳችሁ በመሳተፍ ተጫወቱ።

**ሚና አንድ፡** ስለትራፊክ ህጎች ግንዛቤ የሌለው ተማሪ ሆኖ መንገድ ያለአግባብ ለማቋረጥ ሲሞክር ጓደኛው ጎትቶ ከአደጋ የሚያተርፈው ተማሪ ሆኖ መተወን

**ሚና ሁለት፡** በትምህርት ቤት ውስጥ የትራፊክ ደህንነት ክበብ አባል የሆነና ስለ ትራፊክ ህጎች ለምሳሌ ግራውን ጠብቆ ስለመጓዝ እና መንገድ በአግባቡ ስለማቋረጥ የሚያውቅና ጓደኛውን የሚመክር ተማሪ ሆኖ መተወን

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት አራት፡- በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብቦ መግለጽ

- **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. የእሳት አደጋ የደረሰበት ሰው አጋጥሟችሁ ያውቃል?
2. በቤታችሁ የእሳት አደጋ እንዳይፈጠር የምታደርጉት ጥንቃቄ ምንድን ነው?

- **በንባብ ጊዜ**

ከዚህ በታች ከእሳት አደጋ ስለመጠበቅ የቀረበውን መመሪያ እያነበባችሁ እንዴት እንደምትተገብሩት እያሰባችሁ እራሳችሁን አዘጋጁ፡፡

#### ከእሳት አደጋ መጠበቅ

አብዛኛው የመኖሪያ ቤት እሳት የሚጀምረው ከኩሽና ቤት ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያሉትን ቀላል እርምጃዎች በመከተል ምግብ ሲያበስሉ ደህንነትን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

***<u>መመሪያ 1</u>***

- በምድጃ ላይ ምግብ ሲበስል አጠገቡ መሆን፣
- ነበልባል እሳትን ከቦታ ቦታ አለማንቀሳቀስ፣
- እሳቱ ከ፣ተነሳ ከእንጨት በተሰራ መክተፊያ ወይም ብርድ ልብስ መሸፈን፣
- እሳቱ ፈንድቶ እንዲስፋፋ ስለሚያደርግ የሚቀጣጠለው ዘይት ወይም ስብ ቅባት ከሆነ ለማጥፋት ውሃን አለመጠቀም፡፡

**መመሪያ 2**

**ለመኖሪያ ቤት እሳት መጀመር ብዙ ጊዜ ቤንዚንና ናፍጣ የመሳሰሉ ነዳጆች እንዲሁም ሻማዎች አስተዋፅኦ አላቸው። ይህንን ለመከላከል:-**

- **ሻማዎችን በመስኮት ላይ አለማስቀመጥ፣**
- **ለመኝታ ወደ አልጋ ከመሄድዎ በፊት ወይም ከቤት ከመውጣትዎ በፊት ሻማዎችና ነዳጆችን ማጥፋት፣**
- **ሻማዎችና የዘይት ማቀጣጠያዎች ላይ ህጻናትን ያለ ተቆጣጣሪ ለብቻ አለመተው፣**
- **እሳትን ለማቀጣጠል የሚረዱ ፈሳሾችን (ቤንዚን እና ናፍጣ፣ ወዘተ.) በምንም አለመጠቀም።**

## ተግባር

### ❖ ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ባነበባችሁት መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. በመመሪያ አንድ የቀረቡትን የጥንቃቄ መልዕክቶች ዘርዝሩ።
2. በመመሪያ ሁለት የቀረቡትን የጥንቃቄ መልእክቶች በተመለከተ አንብባችሁ የተረዳችሁትን እጅ በማውጣት ለክፍሉ ተማሪዎች ተናገሩ። መመሪያዎቹንም በየእለቱ በቤታችሁ እራሳችሁንና ቤተሰባችሁን ከአደጋ ለመጠበቅ ተጠቀሙበት።

## ትምህርት አምስት፡- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብቦ ይዘታቸውን መተንተን

### ተግባር

- **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጽሑፉን ከማንበባችሁ በፊት በቃል መልሱ፡፡

1. ኮምፒዩተር አይታችሁ ወይም ነክታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ኮምፒዩተር ምን ለመስራት የሚያገለግል ይመስላችኋል?

- **በንባብ ጊዜ**

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ እያነበባችሁ ማስታወሻ ያዙ፡፡

**የኮምፒዩተር ዘመን እየመጣ ነው**

ዘመናችን የኮምፒዩተር ነው፡፡ የኢንደስትሪ አብዮት በ150 ዓመታት ከዚህ በፊት ዓለም በሺ ዘመናት ያልደረሰችበትን የማምረት፣ የማከፋፈልና የማጓጓዝ ሥራን ማስገኘት ቻለ፡፡ ከኢንደስትሪ አብዮት ወደ ኮምፒዩተር አብዮት የተደረጉ ሽግግሮች ያመጡትን ለውጥ ማጤን ተገቢ ነው፡፡ የኮምፒዩተር ዘመን የኢንደስትሪ አብዮት በመቶ ሃምሳ ዓመት ያስገኘውን ለውጥ በአስርት ዓመታት እጥፍ በሆነ መልኩ ማምረት፣ ማጓጓዝና ማከፋፈል አስቻለ፡፡ የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ ዓለም በሺ ዘመናት ያላየችውን ለውጥ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ያሳካዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የመጭው ዘመን ቴክኖሎጂ ኑሮን ከሥር ከመሠረቱ እየለወጠው ነው፡፡



በአሁኑ ጊዜ በብዙ ኋላቀር ቦታዎች መጻሕፍት ለግዥ የሚቀርቡት፣ በአሳታሚዎች በኩል ማተሚያ ቤት ገብተው፣ ተባዝተው፣ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው፣ ከውጭ አገር የሚመጡ ከሆነ በየብስ፣ በባሕርና በአየር ተጓጉዘው ከዚያም ለየቤተ መጻሕፍቱና የመጽሐፍ መደብሮች ታድለው ነው። መጻሕፍት ለመግዛት ወይ ለማንበብ ሰዎች ወደ መጽሐፍ መደብሮችና ቤተ መጻሕፍት ይሄዳሉ። አሁን ቴክኖሎጂው የለመድነውን አሠራር እየቀየረው ነው። በኮምፒዩተር የተጻፈና ለሕትመት የተዘጋጀ መጽሐፍ ኮምፒዩተር ከሚጠቀም ከአንድ ቦታ በዓለም ላይ ላለ የትኛውም ቦታ በኢንተርኔት ሊተላለፍና ከኮምፒዩተር ጋር በተጣመሩ ዲጂታል ማተሚያዎች በሁሉም ቦታዎች በአንድ ጊዜ በመጽሐፍ መልክ ሊታተም ይችላል።

ይህ ብቻ አይደለም። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከባንክ ገንዘብ ለማውጣትም ሆነ ክፍያ ለመፈጸም ወደ ባንኩ መሄድ ነበረበዎት። ዛሬ እቤትዎ ቁጭ ብለው አልያም በስራ ቦታዎ ሆነው በስልክዎ ይህንን መፈጸም ይችላሉ።

አዳዲስ አሠራሮችን ለመረዳት አሁን ያለንበት ዘመን የመጀመሪያውን አውሮፕላን ያበረሩት ወንድማማቾች ከነበሩበት ዘመን የተሻለ ነው። ሁለቱ ወንድማማቾች አንድ ሰው የምትይዝ አውሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ ሠርተው ሲበሩ ወደፊት አውሮፕላን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አሳፍሮ ይጓዛል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ነገር ግን ከድምጽ በላቀ ፍጥነት የሚበሩ አውሮፕላኖች ይኖራሉ ብሎ

የተነበየን ሰው ሥራ ፊት፣ የማይመስል ነገር ቀባጣሪ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። የዚህ ዓይነቱ አባባል ሳይንሳዊ ልቦለድ የሚል ቅጽል ተሰጥቶትም ነበር።

በዛሬው ዘመን ስጋን በላቦራቶሪ መሥራት ይቻላል የሚለውን በመገናኛ ብዙሃን በተሻለ በማስረዳት ለማሳመን ይቻላል። ብዙዎቻችን በዚህ ዓይነት የተመረተን (የታተመን) ስጋ ሰዎች ለቅምሻ ሲበሉ የተመለከትነው በቴሌቪዥን ነው።

በጥንት ዘመን በበቅሎና በፈረስ ከቦታ ቦታ ይጓጓዝ የነበረው የዓለም ህዘብ በኢንደስትሪ አብዮት የተነሳ መኪና ሲፈበረክ መጓጓዣውን ቀየረ። ለቅንጦት ካልሆነ በቀር በበቅሎና በፈረስ መጓጓዝ በቀረበት ዓለም አሁንም በአገራችን ይህን እየተጠቀምን እንገኛለን። የወደፊቱ የሰው ልጅ መጓጓዣ የሚሆነው ተብሎ የሚገመተው አሁን በሥራ ላይ ውለው በአካባቢ የሚመረቱ ዕቃዎችን ከቤት ቤት ለማጓጓዝ ሊጠቅሙ ይችላሉ የተባሉ ኦቶኮፕተርስ የተባሉ ማጓጓዣዎች ተሰርተዋል። ስለዚህ አንድ ቦታ ላይ የተመረተን ዕቃ ሌላ ቦታ ለሚገኝ ደንበኛ ኦቶኮፕተሩ ላይ ጭናችሁ የመንገዱን አቅጣጫና የሚያርፍበትን ቦታ በኮምፒዩተር ፕሮግራም አስተካክላችሁ ትልካላችሁ። ደንበኛችሁ ኦቶኮፕተሩ ከበራፉ ያስቀመጠለትን ዕቃ ይረከባል።

በጥቅሉ በኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ ዓለም በፍጥነት እየተቀየረች መሆኑን እያየን ነው። እውነት የማይመስሉ ነገር ግን ዓለም እየሰራቻቸው ያሉ በርካታ ስራዎች በኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ እየታገዙ ነገሮችን በሚያስገርም ፍጥነት እየቀየሩ ነው። የሀገራችን አዲሱ ትውልድም ዓይኑን ጥሎ ዓለም ምን እየሰራች እንደሆነ መመልከትና ነገሩን ለመረዳት መሞከር አለበት። ምክንያቱም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሀገሩን የማዘመን እና የተሻለች ማድረግ ነገ የሚረከበው ትውልድ ሀላፊነት ነውና።

(ጥላሁን ጣሰው በ2007 ዓ.ም የመጭው ዘመን ቴክኖሎጂና ኑሮ በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ለማስተማር እንዲያመች ሆኖ የቀረበ)

### ❖ የድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡**

1. ከምንባቡ የተረዳችሁትን በአጭሩ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. ከኢንዱስትሪ አብዮትና ከኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ ዓለምን በፍጥነት እየቀየረ ያለው የትኛው ነው? ምሳሌዎችን ጠቅሳችሁ አብራሩ፡፡
3. አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሰራሮችን ማወቅና በሀገራችን መጠቀም አስፈላጊ ይመስላችኋል? እጅ እያወጣችሁ ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
4. አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሰራሮችን ተረድቶ ሀገርን በማዘመን ሂደት የእናንተ ድርሻ ምን መሆን ያለበት ይመስላችኋል?

## መ መጻፍ

## ትምህርት ስድስት፡- የጽሕፈት ደረጃዎችን መዘርዘር

### ተግባር

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ድርሰት (ጽሕፈት) በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ ነው ወይስ ሂደትን የሚጠይቅ?
2. የጽሕፈት ሂደት ደረጃዎችን ጥቀሱ፡፡

**ማስታወሻ**

የጽሕፈት ደረጃ በጽሑፍ ወቅት የምንከተለው የመጻፍ ሂደት ነው፡፡ ማንኛውም ደራሲ የሚያልፍባቸው የጽሕፈት ደረጃዎች ወይም ሂደቶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

**1. ቅድመ ጽሕፈት /ከመጻፍ በፊት/**

ቅድመ ጽሕፈት ወሳኙ የጽሕፈት ሂደት ሲሆን ደራሲው ድርሰቱን ከመጀመሩ

በፊት የሚያከናውናቸውን ተግባራት የሚመለከት ነው፡፡ እያንዳንዱን የቅድመ መፃፍ ተግባር በተናጠል ለማየት እንሞክራለን፡፡

**ሀ. ርዕስ መምረጥ፡-** ድርሰት ለመጻፍ የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን የሚጻፍበትን ርዕስ ለይቶ መወሰንን ይመለከታል፡፡ የሚመረጠው ርዕስም ጸሐፊው በቂ መረጃ የሚያገኝበትና አዲስ ነገር ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለበት፡፡

**ለ. ርዕስ ማጥበብ፡-** ማለት ብዙ ሀሳብ ሊነሳበት በሚችል ሰፊ ርዕስ ውስጥ ሊነሱ ከሚችሉ ጉዳዮች በአንዱ ላይ ብቻ በማተኮር ጉዳዩን በጥልቀት ለመግለጽ በሚያስችል መልኩ ማስቀመጥ ነው፡፡

**ሐ. የምንፅፍበትን አላማ ማወቅ**

ዓላማችንን ከመጀመሪያው ካወቅን/ከወሰንን/ የምናጠበው ርዕስ ከዓላማችን ጋር የሰመረ፣ የምንሰበስበው መረጃ አላማችንን የሚያሳካ፣ የምንመርጠው የአደጃጀት ስልት ያን አላማ ከግብ የሚያደርስ ወዘተ ይሆናል፡፡

**መ. አንባቢን ማወቅ**

ድርሰት ስንፅፍ አንባቢዎችን እነማን እንደሆኑ ማለትም በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸው ዕውቀት፣ እድሜያቸው፣ ፆታቸው፣ ሙያቸው፣ ከፅሑፋች ጋር ያላቸው ቅርበት ወዘተ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ነው፡፡

**ሠ. መረጃን ማሰባሰብ**

ልንጽፍበት ባቀድነው ጉዳይ ዙሪያ ጠቃሚ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች የምናሰባስብበት ነው፡፡

**ረ. የድርሰታችንን ዋና ሀሣብ መለየት**

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለጽሁፋችን ከሰበሰብናቸው መረጃዎች በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ሀሣቦች ብቻ ለይተን የምንመርጥበት ነው፡፡

**ሰ. የድርሰታችንን አደረጃጀት መወሰን/ ቢጋር መንደፍ/**

በድርሰታችን መገለፅ ያለበትን ዋና ሐሣብ ከመረጥን በኋላ በድርሰቱ ውስጥ በምን ቅደም ተከተል ማቅረብ እንዳለብን የምንወሰወንበት ነው፡፡

**2. ማርቀቅ /መፃፍ**

ማርቀቅ ሀሳብ እንደወረደ በግርድፉ የሚፃፍበት የመጀመሪያው የጽሕፈት ጊዜ ተግባር ነው፡፡ ተግባሩም በቅድመ ጽሕፈት የሰበሰብናቸውን መረጃዎች ስለምንም

ዓይነት ስህተት ሳንጨነቅ በዐረፍተ ነገር መልክ የምናቀናብርበት ነው፡፡

**3. መከለስና አርትኦት ማድረግ**

መከለስ የፃፍነው ድርሰት ያለውን ስህተት ለማስተካከልና የጐደለውን ለመሙላት ስንል እንደገና የምንፅፍበት ሂደት ነው፡፡ በሂደቱም የጻፍነውን መሰረዝ/ማውጣት/፣መጨመር፣ መተካት፣ እንደገና ማደራጀትን የምናከናውንበት ነው፡፡ አርትኦት ደግሞ በፅሑፉ ውስጥ የሰዋስው፣ የሥርዓተ ነጥብ፣ የቃላት ምርጫ፣ የፊደል ስህተት መኖር አለመኖሩን የምናረጋግጥበትና የምናርምበት ነው፡፡

## ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስለጽሕፈት ደረጃዎች የተማራችሁትን መሰረት በማድረግ መልሱ፡፡

1. ቅድመ መጻፍ ደረጃዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. ርዕስ በመምረጥና ርዕስ በማጥበብ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
3. አንባቢን ማወቅ ምን አይነት ጉዳዮችን ያካትታል?
4. የድርሰት አደረጃጀትን መወሰን ምንድን ነው?
5. ማርቀቅ ምንድን ነው?
6. መከለስና አርትኦት መስጠት ምን አይነት ተግባር ነው?

## ሠ ሥነ ጽሑፍ

### ትምህርት ሰባት፡- ግጥም ማንበብ

**ተግባር**

1. ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም መምህራችሁ እንዴት እንደሚያነቡ ተመልከቱና የግጥም አነባብ ስልትን በተከተለ መንገድ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ በየተራ አንብቡ፡፡

## ይኼ ጊዜ

አቻምናም በረረ፣
አምናም ተሻገረ፣
ህጻን እያደገ ልጅ ይጎለምሳል፣
ይጠፋል አሮጌው ወጣትም ያረጃል።
ጊዜ እየደረጀ፣
መስከረም ሲቀባ ቀለም ባመት ባመት፣
አልተወም ማደሱን ያረጀውን ፍጥረት።
ሰው ነው የሚሄደው ጊዜን እየለካ?
ወይንስ ጊዜ ቆሞአል ምንም ሳይነካ?
ምናልባትም ደግሞ አብረው ይሄዳሉ?
አይ አይ አይደለም፣
ወደኋላው ሲቀር ፍጥረት በድካሙ
ጊዜ ይራመዳል ሲቃለል ሸክሙ።

(ገብረክርስቶስ ደስታ፣ 2005፣ ገጽ 6 ለማስተማር እንዲመች ተቀንጭቦ የተወሰደ)

**ማስታወሻ**

ግጥም ውስጥ የቃላት ተመጣጥኖ መቀናበር፣ የድምጾች ተመሳስሎ መደርደር ዜማን ያስገኛል። የአንድን ግጥም ሃሳብ ለማግኘት ይህንን ዜማ ተከትሎ ድምጽን ከፍ አድርጎ ደጋግሞ ማንበብ ይበጃል። ግጥሙን ሳትደነቃቀፉ ካነበባችሁና ዜማው በሚቀሰቅሰው ስሜት ማለትም በሀዘኑ ካዘናችሁ በደስታው ከተደሰታችሁ የግጥሙን አጠቃላይ መንፈስ (ሐሳብ) አግኝታችሁታል ማለት ነው።

2. ቀጣዩን ግጥም መምህራችሁ ባሳዩዋችሁ የአነባብ ስልት መሰረት በየተራ በክፍል ውስጥ ተለማመዱ፡፡ አንዱ ተማሪ ሲያነብ ሌሎቻችሁ እያዳመጣችሁ ስለአነባበቡ ትክክለኛነት አስተያየት ስጡ፡፡

**ያፍ ዘመድ**

ዝም ያለው ዘመዴ እኔ ሳጣጥር፣
ሞተ ቢሉት መጣ አልቅሶ ሊቀበር፡፡
እኔም ሞቼ ሳለሁ ይህንን ስላየሁ፣
በመንፈስ ነድጄ ተቃጥዬ ጨስሁ፡፡
የልቤን እንዳደርስ የእግዜአብሔር ፍቃዱ፣
ሆኖ፣ ተነስቼ እነሱ ሲያረግዱ፣
እንዲህ አልኩት ዘመድ የተባለውን፣
ታምሜ ነበረ ሳጣጥር ማዘን፤
አሁን ክንዴ ክንዴ ቀኝ እጄ ቢሉኝ፣
አሁን የእናቴ ልጅ ወንድሜ ቢሉኝ፣
ከሞትኩኝ በኋላ ምንም አይገባኝ፣
ይልቅ ልተኛበት አታደንቁሩኝ፡፡
ይህን ተናግሬ አንጀቴን አርሼ፣
ወደ መጣሁበት ሄድኩኝ ተመልሼ፡፡

(መንግስቱ ለማ)

# ምዕራፍ ሰባት

# ልዩ ፍላጎት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ታሟላላችሁ፤
- በልዩ ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ጉዳዮችን አዳምጣችሁ ትወያያላችሁ፤
- በሚና ጫወታ ውስጥ ትሳተፋላችሁ፤
- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብባችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ፤
- በሕይወት ተሞክሮዎቻችሁ ላይ ሰፋ ያለ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ማመልከቻ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ።

## ሀ ማዳመጥ

## ትምህርት አንድ፡- ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላት

### ተግባር

ከዚህ በማስከተል መምህራችሁ የአካል ጉዳተኝነት በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ጽሑፉን ከማዳመጣችሁ በፊት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ በቃል መልሱ፡፡

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

1. አካል ጉዳተኝነት ምንድን ነው?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረበው የተጓደለ ጽሑፍ፣ መምህሩ በንባብ በሚያስደምጧችሁ ጽሑፍ መሰረት የሚመለስ ነው፡፡ ከማዳመጣችሁ በፊት የተጓደለውን ሀሳብ የያዙትን አንቀጾች አንብባችሁ ምን ዓይነት መረጃዎች ላይ ማተኮር እንደሚገባችሁ ለይታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

1. ____________ በተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ በንጽሕና ጉድለት፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት፣በአደጋና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል፡፡
2. ሦስተኛው ከሰው ልጅ የአእምሮ አሰራርና የባህሪይ ሁኔታ ጋር የሚዛመደው ________________________ነው፡፡

3. በአንድ ሰው ላይ ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት ሊደርስ የሚችል ሲሆን ይህ ዓይነቱ ውስንነት ________________________ በመባል ይጠራል፡፡
4. የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማህበረሰብ አባል ተቆጥረው የትኛውም______________፣________እና መብቶቻቸው ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡
5. ብዙዎቹ የአካል ውስንነቶች በእርግጥ እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ከመማር__________እና እራሳቸውን ከማስተዳደር የሚያግዱ አይደሉም፡፡
6. የአካል ጉዳተኞች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚታገዱት ________ውስጥ ስር በሰደዱ ኋላቀር አመለካከቶችና በአካባቢ____________ነው፡፡
7. በዘመድ፣ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በጉርብትና፣ በሥራ ቦታና በትምህርት ቤት የሚደርስባቸው __________ ከቆመና ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው እነዚህ ወገኖች በየትኛውም ዘርፍ ሙሉና ____________ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡

## ❖ ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ፡፡

1. የአካል ጉዳት የሚደርሰው በምን ምክንያት ነው?
2. አካል ጉዳኝነትን በስንት መደብ ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡
3. አካል ጉዳተኛ ጓደኛ ቢኖራችሁ በምን ዓይነት መንገድ ታግዙታላችሁ?

## ለ መናገር

### ትምህርት ሁለት፡- በሚና ጫወታ መሳተፍ

**ተግባር**

ተማሪዎች በመምህራችሁ መሪነት አምስት አባል ያለው ቡድን መስርቱና ተከታዩን የመነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሚና ወስዳችሁ ተጫወቱ፡፡

**የመነሻ ሀሳብ**

ተማሪዋ በአንድ እግሯ ላይ የአካል ጉዳት አለባት፡፡ የምትንቀሳቀሰው ዱላ ተደግፋ ነው፡፡ እናት ልጄ ወደፊት ምን ያጋጥማት ይሆን እያለች ትጨነቃለች፡፡ የተማሪዋ ጓደኛ የአካል ጉዳተኛዋን እናት እያየች ታዝናለች፡፡ ይህንንም ለአማርኛ መምህር/ሯ ነገረች፡፡ መምህሩ/ሯ በአካባቢው ያለ ባለሀብት በማነጋገር ለአካል ጉዳተኛዋ ክራንች እንዲገዛላት አደረገ፡፡ ተማሪዋ በተደረገላት ነገር ተደሰተች፡፡

ሚና አንድ፡- የአካል ጉዳተኛ ሆኖ መተወን፡፡

ሚና ሁለት፡- መምህር ሆኖ መተወን፡፡

ሚና ሦስት፡- የአካል ጉዳተኛዋ ጓደኛ ሆኖ መተወን፡፡

ሚና አራት፡- የአካል ጉዳተኛዋ እናት ሆኖ መተወን፡፡

ሚና አምስት፡- ባለሀብት ሆኖ መተወን፡፡

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት ሦስት፡- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ አስተያየት መስጠት

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረበው ጽሑፍ በግልና በዝምታ የምታነቡት ነው። ጽሑፉን ከማንበባችሁ በፊት በቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ።

❖ **ቅድመ ንባብ ጥያቄ**

1. አካል ጉዳተኞች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በተደጋጋሚ የሚያጋጥማቸው ችግር ምንድን ነው?

**የአካል ጉዳተኝነት ፈተናዎች**

ራሄል የልጅነት ውብ እድሜዋን ያሳለፈችው ከእድሜ እኩዮቿ ጋር እንደልቧ ተጫውታ ነው። በተፈጥሮ የተቸራት ብሩህ አእምሮዋ ከቅልጥፍናና ከፈጣን ተፈጥሮዋ ጋር ተዳምሮ በመንደራቸው እጅግ ተወዳጅ ልጅ አድርጓታል። ራሄልና ጓደኞቿ ለልጆች ተብሎ የተከለለ ሥፍራ ባለመኖሩ በአብዛኛው ኳስ የሚጫወቱት አስፋልት ላይ ነው። ከእለታት አንዷ በሆነችው ቅዳሜ ረፋድ ላይ እየከነፈ የሚመጣው መኪና አስፓልት መሀል የገባባትን ኳስ ታቅፋ የምትመለሰዋን ታዳጊ ገጪት። ራሄል በአደጋው ህይወቷን ባትነጠቅም እግሮቿ ተቆርጠው ተረፈች።

ወላጆቿ አጋጣሚው በጣም ቢያሳዝናቸውም ተስፋ ቆርጠው ተስፋዋን ሊነጥቋት ግን አልፈለጉም። ሰባተኛ ክፍል ላይ የቆመው ትምህርቷን በማስቀጠል ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚያደርሷት ቃል ገቡላት።

አባቷ ለልጃቸው የሚሆን ትምህርት ቤት ፍለጋ የጀመሩት ገና ክረምቱ ሳይገባደድ ነበር፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን በሙሉ ዞረው ጠየቁ፡፡ ነገር ግን አልሆነላቸውም፡፡ በዊልቸር ድጋፍ የምትንቀሳቀሰው ታዳጊ ልጃቸው ከሰፈራቸው ራቅ ወዳለ ትምህርት ቤት ሄዳ መማሯ አስቸጋሪ እንደሚሆንባት ቢገባቸውም አማራጭ አልነበራቸውምና ፍለጋቸውን አራዘሙት፡፡ ግን አልተሳካም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ትምህርት ቤቶቹ በተለይም መወጣጫ ደረጃዎቹና መጸዳጃ ቤቶቹ እንደራሄል ያሉ አካል ጉዳተኞችን ለማስተናገድ በሚችሉበት ሁኔታ አለመሰራታቸው ነው፡፡ ተማሪ በመመዝገብ ላይ ያሉ ሠራተኞች ገና የታዳጊዋ አካል ጉዳት ሲነገራቸው ሊመዘግቧት እንደማይችሉ ይነግሯቸዋል፡፡ አባት እያዘኑ ሌላ ትምህርት ቤት ፍለጋ ይወጣሉ፡፡

❖ የራሄል አባት ለልጃቸው ትምህርት ቤት የሚያገኙላት ይመስላችኋል?

የራሄል አባት ለሳምንታት በዘለቀው ፍለጋ የተሳካ ነገር ባለማግኘታቸው ተስፋ ወደመቁረጥ ተጠግተዋል፡፡ በታላቅ ጉጉትና ተስፋ መስከረምን ለምትጠብቀው ታዳጊ ልጃቸው ምን ምላሽ እንደሚሰጧት ግራ ገብቷቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችን የመሰሉ መሰረታዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሁሉንም ዜጋ በእኩል መንገድ ሊያስተናግዱ በሚችሉበት መንገድ ለምን እንደማይገነቡ አጥብቀው ይጠይቃሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ከዚህ ቀደም እምብዛም አሳስቧቸው አለማወቁ ደግሞ በእጅጉ አስገርሟቸዋል፡፡

ይህ ችግር በትምህርት ቤቶች ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ ህክምናና ትራንስፖርትም ዕጣቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ እንደራሄል መማር እየፈለጉ ያልቻሉትን በርካታ አካል ጉዳተኛ ወገኖች መማር ይችሉ ዘንድ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ ከሁላችንም የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

(አዲስ አድማስ፣ ጳጉሜ 3/2004 ለማስተማር እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ)

### ❖ ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1. ራሄል የደረሰባት ችግር ምንድን ነው?
2. ለልጆች መጫወቻ ተብሎ የተከለለ ሥፍራ አለመኖር ለአካል ጉዳት ያጋልጣል? እንዴት?
3. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፎቆችን ሲገነቡ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ምን ማድረግ ይገባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## መ መጻፍ

## ትምህርት አራት፡- አንቀጽ መጻፍ

### ተግባር

በምዕራፍ አራት ላይ ስለአንቀጽ አጻጻፍ የተማራችሁትን በማስታወስ በአካባቢያችሁ ስለምታውቁት በአካል ጉዳተኝነቱ ሳይበገር ሕይወቱን ስለሚመራ ሰው አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

## ትምህርት አምስት፡- የማመልከቻ ደብዳቤ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ደብዳቤ ምንድን ነው?
2. የደብዳቤ ዓይነቶችን ጥቀሱ፡፡

**ማስታወሻ**

የደብዳቤ አይነቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የወዳጅ ዘመድ፣ ማመልከቻ፣ የመስሪያ ቤት፣ የጥሪ ደብዳቤና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህ መካከል በዚህ የክፍል ደረጃ የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍን ትማራላችሁ፡፡

**የማመልከቻ ደብዳቤ፡-** ከግለሰብ ጉዳዩ ወደሚመለከተው ተቋም/ድርጅት የሚፃፍ የደብዳቤ አይነት ሲሆን ግለሰቡ እንዲሆንለት የሚፈልገውን ጉዳይ በደብዳቤው ላይ በማስፈር የሚያቀርብበት ነው፡፡የማመልከቻ ደብዳቤ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- **ቀን፡-** ማመልከቻው የተጻፈበት ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም መፃፍ አለበት፡፡
- **የተቀባይ አድራሻ፡-** መልዕክቱ የሚላክለት ድርጅት ወይም ተቋም ስሙ በትክክል መፃፍ አለበት፡፡
- **የማመልከቻው ርዕሰ ጉዳይ/ጉዳዩ/፡-** የማመልከቻው መልዕክት ስለምን እንደሆነ በአጭሩ የሚገልፅ ክፍል ነው፡፡
- **የማመልከቻው ዋና አካል፡-** የማመልከቻው መልዕክት የሚቀርብበት ዋነኛ ክፍል ነው፡፡ መልዕክቱ በቀጥታ ዋናውን ነጥብ በማንሳት በቀላልና ግልጽ ቋንቋ በመጠቀም መፃፍ ይኖርበታል፡፡
- **መዝጊያ/መደምደሚያ/፡-** የደብዳቤው መልዕክት ተፅፎ ሲጠናቀቅ የሚጻፍ ሲሆን የትህትና ቃላትን በመጠቀም ነው፡፡
- **የአመልካች ስምና ፊርማ፡-** ማመልከቻው ከግለሰቡ የተጻፈ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሰጥ ነው፡፡

## የማመልከቻ ደብዳቤ የሚከተለው ቅርፅ አለው፡፡

ቀን ---------------------------

የተቀባይ አድራሻ

ጉዳዩ፡- ________________________________

---------------------------------- የደብዳቤው መልዕክት-------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------------------------------------…………..በትህትና አመለክታለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፊርማ

የአመልካቹ ስም

**ምሳሌ፡-**

ቀን 18/10 2013

ለዲላ መብራት ኃይል

ዲላ

**ጉዳዩ፡- <u>አዲስ ቆጣሪ እንዲቀየርልኝ ስለመጠየቅ</u>**

አመልካች እኔ ማርቆስ በየነ የዲላ ከተማ ነዋሪ ስሆን ቀደም ሲል ስጠቀምበት የነበረው ቆጣሪ ተደጋጋሚ ብልሽት እየገጠመው የመብራት መቆራረጥ አስከትሎብኛል፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ ይህንኑ ችግር ተረድቶ በአዲስ ቆጣሪ እንዲቀይርልኝ በትህትና አመለክታለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፊርማ

ማርቆስ በየነ

**ተግባር**

የተማራችሁትን የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ከሚገኙ ክበቦች በአንዱ ተሳታፊ ለመሆን የማመልከቻ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# ሱስና መዘዙ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ሱስና መዘዙ የሚለውን ጽሑፍ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፤
- የሱስ መከላከያ ዘዴን በሚመለከት የባለሙያ ምክር አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፤
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ታፈልቃላችሁ፤
- በሱሰኝነት የምታውቁትን ሰው ታሪክ ትናገራላችሁ፤
- በተማሪዎች ፊት ክርክር ታደርጋላችሁ፤
- አንብባችሁ በተረዳችሁት መሰረት ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፤
- የሕይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፤
- ምሳሌያዊ ንግገሮችን ትጽፋላችሁ፡፡

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር መናገር

**ተግባር 1**

**ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ “ሱስና መዘዙ” በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ በንባብ ያስደምጧችኋል፡፡ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ሱስ ምንድን ነው?
2. ሰዎች ሱሰኛ በመሆናቸው ምክንያት ምን ሊደርስባቸው ይችላል?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

**መምህሩ የሚያነቡላችሁን ጽሑፍ እያዳመጣችሁ በመሀል ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

- **ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መምህሩ ያስደመጧችሁን ታሪክ መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ለደሰና ውድቀት መነሻው ምን ነበር?
2. ደሰና ሱሰኛ በመሆኑ ምክንያት የደረሰበት ችግር ምንድን ነው?

**ተግባር 2**

**የባለሙያ ምክር አዳምጦ መናገር**

**መምህራችሁ ከሱስ ለመላቀቅ የሚረዱ የባለሙያ ምክሮችን በንባብ ሲያቀርቡላችሁ አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ከሱስ ለመላቀቅ የሚያግዙ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

ለ. ከሱስ ለመላቀቅ ያግዛሉ ተብለው በቀረቡት ዘዴዎች ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. የከፋ የሱሰኝነት ችግር በህክምና እርዳታ ሊፈታ ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁ? ምክንያታችሁን ተናገሩ፡፡

## ለ መናገር

### ትምህርት ሁለት፡- በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ማጠቃለልና ታሪክ መናገር

**ተግባር**

1. ቀደም ሲል በማዳመጥ ክፍለ ትምህርት ሱስና መዘዙ በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ታሪክ መነሻ በማድረግ ፍሬ ሀሳቡን አጠቃላችሁ በቃል አቅርቡ፡፡
2. በአካባቢያችሁ በሱሰኝነቱ የምታውቁትን ሰው ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡ ሌሎቻችሁ ደግሞ ከጓደኞቻችሁ ያዳመጣችሁትን ታሪክ ጠቅለል አድርጋችሁ እጅ እያወጣችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ትምህርት ሦስት፡- የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ

**ተግባር**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ክርክር ምንድን ነው?
2. በክርክር ሂደት ተከራካሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው?

**ማስታወሻ**

በክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ ሂደት በቅድሚያ ርዕስ መምረጥና ቀን መወሰን ቀጥሎም በክርክሩ ወቅት አሸናፊ ሆኖ ለመገኘት በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ከክርክሩ በፊት፡-**

1. ለክርክሩ የሚያግዙ መረጃዎችን ከጽሑፍ ወይም ሰዎችን በመጠየቅ መሰብሰብ፤
2. የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፤
3. የመከራከሪያ ሀሳቦችን የሚያጠናክሩ ጭብጦችን መምረጥ፤
4. ጠንካራ ማጠቃለያ ሀሳብ ማዘጋጀት፡፡

**በክርክሩ እለት፡-**

1. ርዕሱን ማስተዋወቅ፤
2. ሀሳብን በተረጋጋ ስሜት መግለጽ፤
3. የሌላውን ተከራካሪ ሀሳብ በተረጋጋ ስሜት ማዳመጥ፤
4. በክርክሩ ወቅት የሚቀርቡ ሀሳቦች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**የዳኛ ተግባር**

1. ሁለቱ ተከራካሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲናገሩ ማድረግ፣
2. ተከራካሪዎች የሚጠቀሙትን ሰአት መቆጣጠር፣
3. በክርክሩ ያሸነፈውን ቡድን ማሳወቅ፡፡

## ተግባር

ከዚህ በታች ለክርክር መነሻ የሚሆን አጭር ታሪክ ቀርቦላችኋል፡፡ ታሪኩን አንብባችሁ እንዲያከራክራችሁ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ተከራከሩ፡፡

### የክርክር መነሻ ታሪክ

መንገሻ እና አስቴር በጣም የሚዋደዱ አስዋይና ታታሪ ጥንዶች ናቸው፡፡ ትዳር ከመሰረቱ ሰባት አመታቸው ነው፡፡ የትዳራቸው በፍቅር መድመቅ ከታታሪነታቸው ጋር ተደምሮ በመንደሩ ሰዎች እንዲወደዱና እንዲከበሩ አድርጓቸዋል፡፡ መንገሻና አስቴር ጥሩ ንብረትም አፍርተዋል፡፡ በመሆኑም በትዳራቸው በጣም ደስተኞች ናቸው፡፡

እነዚህ ጥንዶች በኑሮአቸው ደስተኛ ቢሆኑም ልጅ አለመውለዳቸው ግን አሳስቧቸዋል፡፡ ሁኔታው የመንገሻን እናትም በጣም እያሳሰባቸው ነው፡፡ ከድህነት ጋር እየታገሉ ያሳደጉት ብቸኛ ልጃቸው ልጅ ወልዶ አያት እንዲያደርጋቸው አጥብቀው ሲመኙ ሰባት አመት ሞላቸው፡፡

ከአመት አመት ለውጥ ማየት ያልቻሉት መንገሻና አስቴር ወደ ህክምና ሄደው ለመመርመር ወሰኑ፡፡ በምርመራው ውጤት አስቴር በተፈጥሮ መውለድ የማትችል መሆኗን አወቁ፡፡ በሰአቱ ሁሉም ተደናግጠው ስለነበር አስቴርን

በማጽናናት ላይ አተኮሩ። በተለይ ባለቤቷ በሆነው ነገር ጨርሶ እንዳይሰማት ሲመክራት ከረመ።

ውሎ አድሮ ግን የእናቱ ውትወታ በዛበት። በየዕለቱ "አንተ ለኔ አንድ ልጅ ነህ፤ ከመሞቴ በፊት ወልደህ የልጅ ልጄን እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ፤ ያለበለዚያ በልጅ ፍቅር ልቤ በሀዘን መሰበሩ ነው" ይሉታል። በሌላ በኩል ሊያጣው የማይፈልገው ለባለቤቱ ያለው ጥልቅ ፍቅርና አክብሮት አዕምሮውን ይጎተተዋል።

መንገሻ ምን ያድርግ፤ የቱ ነው ትክክል? የሚወዳቸውን እናቱን ምኞት ለማሳካትና ልጅ ወልዶ ለመሳም አስቴርን ፈቶ ከሌላ ሚስት መውለድ ወይስ የትዳሩን ዘመን በደስታ ያኖረችውንና መውለድ ባለመቻሏ አዕምሮዋ የተጎዳውን የባለቤቱን ስሜት ጠብቆ የራሱንና የእናቱን ፍላጎት ችላ ብሎ መተው?

(ምንጭ፡- ከአዘጋጆቹ)

## ሐ ማንበብ

### ትምህርት አራት፡- አንብቦ መረዳት

**ተግባር**

❖ **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ሱስ የሚያሲዙ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ በሱሰኝነት የምታውቁት ሰው አለ? ካለ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

❖ **በንባብ ጊዜ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን እያነበባችሁ መልሱ።**

1. በሀገራችን የተለመዱ አደገኛ ሱስ አምጪ ነገሮችን ዘርዝሩ።

2. በሱስ ምክንያት ጉዳት የሚደርስባቸውን የሰውነት ክፍሎች ዘርዝሩ።

## ሱስና ሱሰኝነት

ሱስ ማለት አንድ ነገር ተደጋግሞ እንዲወሰድ የሚገፋፋ ሥር የሰደደ ልምድ ወይም ሁኔታ ነው። አንድ ሰው ጉዳት እንደሚያስከትልበት እያወቀ ይህን ልምዱን ማቆም ካልፈለገ ወይም ካልቻለ ሱሰኛ ሆነ ይባላል። እንደ ቡና፣ሻይና ኮካኮላ መጠጦች ሱስ የማስያዝ አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በአገራችን የተለመዱ በአደገኛነታቸው ሱስ አምጪ ከሚባሉት ደግሞ የአልኮል መጠጦች፣ትንምባሆ ጫትና ሌሎች አደንዛዥ ዕጾች ይጠቀሳሉ።




ብዙ ምርምሮች እንደሚያረጋግጡት ሱስ አምጪ ነገር ሲወሰድ በአእምሮ ላይ የሚፈጥረው የደስታ፣የእርካታና የድል ስሜት በሱስ ለመያዝ ዋናው ምክንያት ነው። ይህ የአእምሮ ሁኔታ ሱስ አምጪው ነገር ያለማቋረጥ እንዲወሰድ ይገፋፋል። መጠኑንም እንዲጨምር ያስገድዳል።

ሱሰኛው በዚህ ከቀጠለ የሚወስደው ሱስ አስያዥ ኬሚካል በሰውነቱ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ስለሚቆይ አእምሮውም ሆነ አካሉ ለነገሩ ፍጹም ተገዢና እስረኛ ይሆናል፡፡

የአልኮል መጠጦች ጫትና ትንባሆ ለረጅም ጊዜ ሲወሰዱ ጉበትን፣ልብንና ሳንባን ይጎዳሉ፡፡ ለደም ብዛት ለተለያዩ የካንሰር ዓይነቶች፣ለአእምሮና ለነርብ ህመም ያጋልጣሉ፡፡ እንዲሁም ሌሎች አካላዊ፣አእምሮአዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ያስከትላሉ፡፡ ስለዚህ ሱስን ከሚያስከትሉ ነገሮች እራሳችንን በመጠበቅ አእምሮአዊና አካላዊ ጤናችንን ከጉዳት ልንከላከል ይገባል፡፡

(ከቀድሞው የ7ኛ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መጽሐፍ ከተወሰኑ ለውጦች ጋር የተወሰደ፡፡)

❖ **ድህረ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ለሰዎች በሱስ መያዝ ዋናው ምክንያት ምንድን ነው?
2. ሱስ በጤንነት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?
3. ከሱስ እንዴት መጠበቅ ይቻላል?

## መ መጻፍ

## ትምህርት አምስት፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ

**ተግባር**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የሕይወት ታሪክ ምንድን ነው?
2. በሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ማስታወሻ**

**የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ**

የሕይወት ታሪክ  የራስ የሕይወት ታሪክና የግለሰብ (የሌላ ሰው) የሕይወት ታሪክ በመባል በሁለት ይከፈላል።

1. የራስ የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ የሚከተሉትን ማካተት ያስፈልጋል።
   - የትውልድ ሥፍራንና የትውልድ ዘመንን መጥቀስ፣
   - ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መጻፍ፣
   - የትምህርት ደረጃን መግለጽ፣
   - የተፈጸሙ ጉልህ ተግባሮችና አስተዋጽኦዎችን መዘርዘር፣
   - ታሪክን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
   - ታሪክን  ቀላልና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ።
2. የግለሰብ የሕይወት ታሪክ የሚከተሉትን ያካትታል።
   - ታሪኩ ስለሚጻፍለት ግለሰብ የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅና የተጻፉ ጽሑፎች ካሉ በማንበብ ማስረጃ መሰብሰብ፣
   - የተሰበሰበውን የግለሰብ ታሪክ በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
   - የግለሰቡን ታሪክ ቀላልና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ጽፎ ማቅረብ፣
   - ታሪኩን ማጠቃለል

## የግል የሕይወት ታሪክ ምሳሌ

ስሜ ከድጃ መሀመድ ይባላል፡፡ የተወለድኩት በ1983 በደቡብ ክልል ሀላባ ከተማ ነው፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩትም እዛው ሀላባ ነው፡፡ የማትሪክ ፈተና በምፈተንበት ዓመት አባቴ ታሞ ሆስፒታል ገብቶ ነበር፡፡ ፈተናውን ለመጨረስ አንድ ቀን ሲቀረኝ የታመመው አባቴ ማረፋን ሰማሁ፡፡ በወቅቱ የተደናገጥኩ ቢሆንም አባቴ በሕይወት እያለ ጠንክሬ ተምሬ እንደማኮራው ይመክረኝ የነበረውን በማስታወስ እንደምንም ተረጋግቼ በአባቴ የቀብር ቀን የቀረኝን ፈተና ተፈተንኩ፡፡ የፈተና ውጤቱ ሲመጣ ለዩኒቨርስቲ ማለፌን አረጋገጥኩ፡፡ ከዚያም በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በኮምፒዩተር ምህንድስና የትምህርት ዘርፍ ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩ፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ የትምህርቴ ውጤት አበረታች ሆኖ ሳገኘው የበለጠ ለመስራት ተነቃቃሁ፡፡ አባቴ በመሞቱ ምክንያት የቤተሰቡ ሙሉ ሀላፊነት እናቴ ላይ በመውደቁ የምትልክልኝ ገንዘብ አልነበራትም፡፡ ይሁን እንጂ ህልሜን እያሰብኩ ትምህርቴን ከነችግሮቹ በጽናት ተቋቁሜ በጥሩ ውጤት ቀጠልኩ፡፡ ያ ሁሉ አልፎ ዛሬ ከሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ከትምህርት ክፍሉ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ለመሆን በቅቼአለሁ፡፡

**ተግባር**

**ከላይ በቀረበው የግል የሕይወት ታሪክ ምሳሌ መሰረት የራሳችሁን የሕይወት ታሪክ ጻፉ።**

## ሠ ሥነ ጽሑፍ

## ትምህርት ስድስት፡- ምሳሌያዊ ንግግሮች

**ተግባር**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ምሳሌያዊ አነጋገር ምንድን ነው?
2. ከምታውቋቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁለቱን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ማስታወሻ**

ምሳሌያዊ ንግግሮች በአጭር ቅርጽ የሚቀርቡ እና ጥልቅ መልዕክት የሚያስተላልፉ የስነ ቃል ዘርፎች ሲሆኑ የሚገቡት በንግግሮች መሀል ነው።

ምሳሌ፡-

1. ሆድና ግንባር አይሸሸግም።
2. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ።
3. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው።
4. ለመልካም ሰው ዋጋ አነሰው።
5. ለገበሬ መልካም በሬ።

**ተግባር**

1. **የሚከተሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል፡፡

ለ. የበላ በለጠኝ ፤የሮጠ አመለጠኝ፡፡

ሐ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፡፡

መ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር፡፡

ሠ. መልካም ተመኝ መልካም እንድታገኝ፡፡

ረ. ሠርቶ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ፡፡

2. **የሚከተሉትን ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮች አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. መስከረም በአበባ__________________፡፡

ለ. ሠርገኛ መጣ_____________________፡፡

ሐ. ማን ያውራ የነበረ__________________፡፡

መ. መብል ያለመጠጥ ________________፡፡

ሠ. ሲሮጡ የታጠቁት__________________፡፡

3. በአካባቢያችሁ ከሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች አስር የሚሆኑትን ከሚያስተላልፉት መልዕክት ጋር በደብተራችሁ ጽፋችሁ አምጡ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ሀገር በቀል ዕውቀቶች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት በማድረግ ልምድ ትለዋወጣላችሁ፤
- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትናገራላችሁ፤
- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ በሚታዩ የንግግርና የሰላምታ አቀራረብ ሁኔታዎች ላይ ልምድ ትለዋወጣላችሁ፤
- ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- በጠንካራ ሰራተኝነት ባህል ላይ ትኩረት ያደረገ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፤
- የተረቶችን ዋና ሀሳብ ትናገራላችሁ፤
- አፈ ታሪኮችን ትናገራላችሁ።

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት ልምድ መለዋወጥ

**ተግባር**

መምህራችሁ የዲዚ ብሔረሰብ ባህላዊ ዳኝነት በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ጽሑፍ ከማዳመጣችሁ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡

- **ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ከሀገር በቀል ዕውቀቶች አንዱ የሆነው ባህላዊ ዳኝነት ምንድን ነው?
2. ባህላዊ ዳኝነት ጥቅሙ ምንድን ነው?

- **በማዳመጥ ጊዜ**

**መመህሩ የሚያነቡላችሁን ምንባብ እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻችሁ ጻፉ፡፡**

- **ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መምህሩ ያስደመጧችሁን ታሪክ መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡**

1. ካዳመጣችሁት ባህላዊ የዲዚ የእርቅ ሥርዓት ምን ተማራችሁ?
2. ያዳመጣችሁትን የዲዚ ብሄረሰብ የእርቅ ሥርዓት ጠቅለል አድርጋችሁ በቃል ተናገሩ፡፡
3. በምትኖሩበት አካባቢ ግጭቶችን ለመፍታት የሚያገለግሉ ባህላዊ የእርቅ ሥርዓቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

4. ቀደም ሲል መምህራችሁ ባስደመጧችሁ የዲዚ ብሔረሰብ የእርቅ ሥርዓትና እናንተ አካባቢ ባለው የእርቅ ሥርዓት አተገባበር ላይ ያሉ ልዩነቶችንና ተመሳስሎዎችን ተናገሩ፡፡

## ለ ማንበብ

### ትምህርት ሁለት፡- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገር

**ተግባር**

**ቀጥሎ የቀረበው ጽሑፍ በግላችሁ የምታነቡት ነው፡፡ ከማንበባችሁ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

❖ **ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. በሀገር በቀል ዕውቀት ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. የሀገር በቀል ዕውቀቶች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

## ሀገር በቀል ዕውቀት

ሀገር በቀል ዕውቀት ማለት በውስን አካባቢዎች ላይ በኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ዙሪያ ላሉ ክፍተቶች መፍትሔ ይሆኑ ዘንድ ባህላዊ በሆነ መንገድ በአንድ ወይም በተወሰኑ ሰዎች የሚመነጭና የሚተገበር ዕውቀት ነው፡፡ የማህበረሰብ ዕውቀት በብዙ ዘመናት የዳበረና በባህል ውስጥ ሰርጾ ከትውልድ ትውልድ በታሪክ፣በዘፈን፣በአባባል፣ በእምነት እና በሌሎች መንገዶች በአካባቢው ቋንቋ የሚተላለፍ ነው፡፡ ዕውቀቶቹ በተገኙበት ቦታ ምንጭ ለሆኑት ግለሰብና ቤተሰብ የተሰጠ ልዩ ጥበብ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአብዛኛው ግን በጊዜ ሂደት እየተለመደና እየተስፋፋ ሲመጣ የማህበረሰቡ የጋራ ንብረት ይሆናል፡፡



በሀገራችን በግብርናው ዘርፍ ጤፍ ፣ቡና፣እንሰትና ሌሎች አዝዕርትን የማላመድ እንዲሁም ከነዚህና ሌሎች ተክሎች ምግብና መጠጥ የማዘጋጀት ሂደት በሌሎች ሀገራት ያልተለመደና የማህበረሰባችን የፈጠራ ውጤት ነው። በአለም ላይ የሚገኙ አርሶ አደሮች ለረጅም አመታት የእርሻ ሥራቸውን በእጅ በሚሰሩ መሳሪያዎች በሚጠቀሙበት ጊዜ የእኛ ማህበረሰብ የፈጠራ ክህሎት በታከለበት ባህላዊ አስተራረስ ዘዴ ማለትም በሬ ጠምዶ የእርሻ ሥራውን ያከናውን ነበር። በተመሳሳይ የኮንሶና አካባቢው ህብረተሰብ ትሩፋት የሆነው የእርከን ሥራ ችግር ፈቺ እና ውጤታማ የሆነ የሀገር በቀል የአፈርና የውሃ ጥበቃ ዘዴ ነው። እነዚህ ተግባራት የማህበረሰባችንን የፈጠራ ችሎታ የሚያሳዩ ናቸው።

### ❖ እስካሁን ከአነበባችሁት ምን ተረዳችሁ?

ዘመናዊ ህክምና ባልተስፋፋባቸው ቀደም ባሉ ጊዜያትም ሆነ ዘመናዊ ህክምና እየተስፋፋ በመጣበት በአሁኑ ሰዓት የማህበራችን ባህላዊ ህክምና እና መድሀኒቶችን የመጠቀም ዝንባሌው በጣም ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም ባህላዊ ህክምናና መድሀኒቶች በአቅራቢያ ስለሚገኙ የገንዘብ አቅምን የማይፈትኑ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታመኑ በተግባርም ፈዋሾች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ የህክምና ተክሎችን በአትክልት ቦታ የመትከል ልምድ አለው። በተጨማሪም ዘመናዊ የእንስሳት ህክምና ተደራሽ ባልሆነበት ዘመን አብዛኛው የሀገሪቱ ከብት ባለቤት ባህላዊ ሀኪሞችና ቀማሚዎች ከሚሰጡት አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆን ቆይቷል።

የሀገር በቀል ዕውቀቶቹ ባለቤቶችና አዋቂዎች ዕውቀቱን መጠቀማቸውን እንዲቀጥሉ ማበረታታት፤ለንግድ ዓላማ ለሚውሉ የሀገር በቀል ዕውቀትና

ምርቶች ከለላ መስጠት፣እንዲሁም የሀገር በቀል ዕውቀትን መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ የፈጠራ ሥራዎችን ማበረታታትና ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። ማህበረሰቡ የፈጠራ ባለቤትነቱ ተረጋግጦለት የፈጠራ ክህሎቱን ለልማት የሚያውልበት መንገድ ሊመቻችለት ይገባል። እንዲሁም የዕውቀቱ ባለቤት የሆኑት ግለሰቦችና ማህበረሰቦች መካከል የልምድ ልውውጥ እና የንግድ ትስስር እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው።

(ከሳይንስና ቴክ. ቅጽ 2፣2007 ለማስተማር እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

**ተግባር**

❖ **ድህረ ንባብ ጥያቄዎች**

**በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየተወያያችሁ መልሱ።**

1. የማህበረሰብ ዕውቀት ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፈው እንዴት ነው?
2. የኮንሶ ማህበረሰብ ሀገር በቀል ሀብት የሆነው የእርከን ሥራ ምን ዓይነት ችግሮችን መፍታት ችሏል?
3. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ባህላዊ የህክምና ዓይነቶችና ለየትኞቹ በሽታዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተናገሩ።

## ሐ መናገር

### ትምህርት ሦስት፡- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ መናገር

**ተግባር**

ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ ምን ዓይነት የቋንቋ አጠቃቀም እንደሚኖራችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ልምዳችሁን ተለዋወጡ።

1. በእድሜ ትልልቅ ከሆኑ ሰዎች ጋር ሰላምታ መለዋወጥ።
2. ሀዘን ቤት ሄዶ ሀዘንተኞችን ማስተዛዘን።
3. አራስ ቤት ሄዶ ወላድ መጠየቅ።

## መ መጻፍ

## ትምህርት አራት፡- ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ድርሰት ምንድን ነው?
2. የምታውቋቸውን የድርሰት ዓይነቶች ተናገሩ።

**ማስታወሻ**

የድርሰት ዓይነቶች በዋናነት በአራት ይከፍላሉ። እነሱም፡-

1. **ተራኪ ድርሰት፡** ባለፈ ጊዜ ውስጥ የተከናወኑ ድርጊቶችንና ሁነቶችን እንደአፈጣጠራቸው እንዲህ ሆነ ወይም ተደረገ በማለት በቅደም ተከተል የሚተርክ ነው።
2. **ስዕላዊ ድርሰት**፡ በቦታው ተገኝተን ያላየነውን ነገር በቃላት አማካይነት እንዳየን፣ እንደሰማን፣ እንዳሸተትን፣ እንደዳሰስን፣ ወዘተ. እንዲሰማን አድርጎ በአእምሮአችን ምናባዊ ምስል የሚፈጥር ነው።
3. **ገላጭ(አስረጂ) ድርሰት፡** የነገሮችን ምንነትና የአሰራር ቅድም ተከተል በምሳሌዎች አስደግፎ የሚያብራራ ነው።
4. **አመዛዛኝ (አወዳዳሪ) ድርሰት**፡ ይህ የድርሰት ዓይነት ሀሳቦችን በማመዛዘንና በማወዳደር የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው። አመዛዛኝ ድርሰት አንባቢውን ወይም አድማጩን የአንድን ነገር እውነትነት ወይም ሀሰትነት

ለማሳመን ጥረት ያደርጋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት አራት የድርሰት አይነቶች የገላጭ (አስረጂ) ድርሰት ምሳሌን እንመልከት፡-

## ጠንካራ የሥራ ባህል

ጠንካራ የሥራ ባህል ማለት ህዝብ ሰርቶ ለመኖር ያለው ጠንካራ ፍላጎትና ልምድ ሲሆን ሰራተኞች ያላቸውን የመስራት ፍላጎትና በሙያው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ያላቸው ቁርጠኝነት ማለት ነው፡፡ ስራ የሰው ልጆች ሁሉ የመኖር ዋስትና ስለሆነ ጠንክሮ ከሰሩ ከራስ አልፎ የቤተሰብንና የአካባቢን ኑሮ ለመለወጥ ወደሚያበቃ ታላቅ ደረጃ ያሸጋግራል፡፡

ስራ ከአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ላይ ተመስርቶ ከቀላል ነገር በመጀመር ጠንክሮ ከተሰራ ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማደግ ያስችላል፡፡ ጠንክሮ መስራት ሲባል በተሰማሩበት የስራ መስክ የተሻለ የምርት ውጤትን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን የስራ ሰዓትን በማክበር፣ ሙያዊ ስነምግባርን በመላበስና የምርት ጥራትን በማሳደግ ጭምር ይገለፃል፡፡

ጠንካራ የስራ ባህል ስራን አለመናቅና ጊዜን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ለራስና ለሃገር ያለውን ጠቀሜታ በተግባር ማሳየት ማለት ነው፡፡ ስራን አለመናቅ ሲባል የትኛውንም የስራ አይነት በእኩል ደረጃ መመልከትና ያገኙትን ስራ ሳይንቁ መስራት ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ የስራ አይነት ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይባል ትኩረት አግኝቶ ከተሰራ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ትንሽ ነው የሚባል አንድ ስራ ተገቢውን ትኩረት ካገኘ ነገ የሚሰራውን ሰው ከፍ ወዳለ እና ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል፡፡

ስራን ሳይንቁና ትንሽ ነው በማለት ሳያማርጡ በመስራት ለውጤት የበቁ ዜጎች ብዙ ናቸው፡፡ ስራን መናቅ አይገባም፤ ሁሉም ስራ በጥሩ ሁኔታ ሊከናወን የሚችለው ጊዜን በማቀድና ለወጣው የስራ ዕቅድ ራስን በማስገዛት ነው፡፡ የጊዜን አጠቃቀም በማወቅ ጠንክሮ የሚሰራ ዜጋ በቤተሰቡም ሆነ በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል፡፡

**ተግባር**

በመምህራችሁ መሪነት ቡድን መስርታችሁ በቀረበው ምሳሌ መሰረት በጠንካራ ሰራተኛነቱ አርአያ የሆነ አንድ ሰው መርጣችሁ ሦስት አንቀጽ ያለው ገላጭ ድርሰት እቤታችሁ ጽፋችሁ አምጡ፡፡

## ሠ ሥነ ጽሑፍ

### ትምህርት አምስት፡- የተረቶችን ዋና ሀሳብ መናገር

**ተግባር**

ቀጣዩን ጥያቄ በቃል መልሱ፡፡

1. ተረት ምንድን ነው?

**ማስታወሻ**

ተረት እያዝናና ሥነ ምግባርን የሚያስተምር በዝርው ቅርጽ የሚቀርብ የሥነቃል ዓይነት ነው፡፡ ተራቹ "ተረት ተረት" ብሎ አድማጭ ደግሞ የመሰረት ወይም "የላም በረት" ብለው ይጀምራል፡፡ ተረቱ ሲነገር በየመሀሉ አድማጮች እሺ ከዚያስ ምን ሆነ? እያሉ የሚያዳምጡበትና ተረቱ ሲያበቃ "ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" ተብሎ የሚጠናቀቅ ነው፡፡

## ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረበውን ተረት አንብባችሁ የተረቱን መልዕክት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### ስስት ይዳርጋል ለሞት

በድሮ ዘመን በአንድ ሀገር ረሀብ መጥቶ ሰው ሁሉ የሚበላው የሚጠጣው አጥቶ ያልቅ ጀመር፡፡ ሰው ሁሉ በየዱሩና በየጫካው ፍራፍሬና ሥራ ሥር እየፈለገና አውሬም እያደነ ይበላ ነበር፡፡ በዚህ የረሀብ ዘመን ባልና ሚስቱ ጫካ ውስጥ ገብተው የሚበላ ነገር ሲፈልጉ ሚስቲቱ አንድ አጋዘን ሰው እንደመጣበት አይቶ በመበርገግ ወደዱር ሲገባ አየችው፡፡ ሴትዮዋ አጋዘኑን እንዳየችው "ኧረ አንድ አጋዘን ከዚያ ዱር ውስጥ ሲገባ አየሁት!" በማለት ለባሏ ነገረችው፡፡ ባልየውም "እንዴ! ምን ሆነሻል ? በመጀመሪያ ያየሁት እኔ አይደለሁም እንዴ?" አለና ድርቅ አለባት፡፡ እሷም "እሺ ካየኸው ጥሩ!" አለችና በሆዷ "ምን አስጨነቀኝ ምን ጊዜም እኔ አየሁት እሱ አየው ለውጥ የለውም፡፡ ቢገድለው ሥጋው የራሳችን ነው፡፡ ብቻ እንዳያመልጥ" በማለት "እንዳያመልጥ! ቀስ ብለህ በዚያ አልፈህ ኮሽታ ሳታሰማ በጦር ውጋው" አለችው ባሏን፡፡

ባሏም ቀስ ብሎ አቅጣጫ ቀይሮ አጋዘኑ ከተደበቀበት ዱር ተጠጋና ጦሩን በመወርወር ወጋው፡፡ አጋዘኑም ወደቀ፡፡ ወዲያው ቆዳውን ገፈው ከጨረሱ በኋላ ባልዬው "ቀድሜ ያየሁት እኔ ስለሆንኩ ሥጋውን እኔ ብቻ ነኝ መብላት ያለብኝ" በማለት ሚስቱን እንዳትበላ ከለከላት፡፡ እሷም "እሺ!" አለችው፡፡ አቶ ባል ሥጋውን ከበላ በኋላ "ውሃ ጠማኝ አንቺስ አልጠማሽም እንዴ?" በማለት ጠየቃት፡፡ ሚስቲቱም "አዎ ጠምቶኛል" አለችው፡፡ ከዚያም ባሏ ሥጋውን በቆዳው በመጠቅለል ተሸክሞ ውሃ ሲፈልጉ ሚስቲቱ ኧረ ያ የውሃ ጉድጓድ ነው መሰለኝ በማለት ማስተዋል ጀመረች፡፡ እሱም ንግግሯን እንደሰማ እንዴ እኔ እኮ ነኝ

መጀመሪያ ጉድጓዱን ያየሁት በማለት ወደጉድጓዱ አቅጣጫ ተመለከተ፡፡ ኋላም ሥጋውን ጠብቂ አላትና በቆዳ ጠቅልሎ የተሸከመውን ሥጋ አስቀምጦ አንድ ቁራሽ ሥጋ እንዳትነኪ ብሎሎ ፊቱን ወደሷ በማዞር እሷን እያየ ወደኋላ ወደ ውሃው ጉድጓድ መሄድ ጀመረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሚስቱ ሥጋውን እንዳትበላበት የኋሊት ወደ ውሃው በመሄድ ላይ እንደነበረ ከጉድጓዱ አፋፍ ደርሶ እግሩ እነደረገጠ ርብርቡ ተንዶ አቶ ባል ተሰባብሮ ከውሃ ውስጥ ገብቶ ውሃ ጠጥቶ ሞተ ይባላል፡፡

(ባይለየኝ ጣሰው፣ 1995፡፡ ከገጽ 163-164)

2. በአካባቢያችሁ ተረት መናገር የሚችሉ ሰዎችን አፈላልጋችሁ አንድ ተረት ጽፋችሁ ተረቱን በየተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡ በማስከተልም ከተረቱ ምን እንደተማራችሁ ግለጹ፡፡

## ትምህርት ስድስት፡- አፈ ታሪኮችን መናገር

### ተግባር

ቀጣዩን ጥያቄ በቃል መልሱ፡፡

1. አፈ ታሪክ ምንድን ነው?

**ማስታወሻ**

አፈ ታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር የስነ ቃል ዓይነት ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ በመነሳት ስነ ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚቀርብ ነው። ይህ የስነ ቃል ዓይነት በማህበረሰቡ ታሪክ በእውነት ተፈጽመዋል በሚባሉ ታሪካዊ ክንውኖች ላይ በመመስረት ስለ ንጉሶች፣ ጦርነቶች፣ ጀግኖች፣ ስለከተሞች ስያሜ፣ ወዘተ. ይነገራል።

**ምሳሌ፡-**

## አፈ ታሪክ

የአጼ ልብነ ድንግል አባት በጊዜያቸው እጅግ የታወቁና የተከበሩ ገዢ ነበሩ። አንድ ቀን የኮሶ መድሀኒት ለመጠጣት እቤት ይውላሉ። ይህንኑ መድሀኒት አሰናድታ እንድታጠጣቸው መልከ ቀናዋ የቤት አገልጋይ ተቀምጠው በነበረበት ማረፊያ ቤት ገባ ወጣ እያለች ስታገለግላቸው ሳለ በተፈጠረው አጋጣሚ ከሳቸው ልጅ ትጸንሳለች። የአገልጋይቱን ሆድ መግፋት ያዩ ሚስትም እሷን በማስገረፍ ሚስጢሯን እንድታወጣ ያደርጋሉ። ይህ ሚስጢርም ከተጋለጠ በኋላ ቤተዘመድ ሁሉ በተፈጠረው ውርደት በመቆጨት የሚወለደው ልጅ የአባቱ አልጋ ወራሽ እንዳይሆን በመስጋት ሴራ ይጠነስሳሉ። በተጠነሰሰው ሴራ መሰረት አገልጋይዋ የምትወልደው ህጻን አይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ በማለት ሚስትየዋ የአገልጋዩዋን ሆድ በሚስጢር በተልባ እንዲታሽ ያደርጋሉ። ሴራው እንዲሳካ በተደጋጋሚ የእርጉዟን አገልጋይ ሆድ በተልባ የማሸቱ ተግባር ይቀጥላል። በመጨረሻም ህጻኑ ሲወለድ አይነ ስውር በመሆን ፈንታ የተለየ ውበት ያላቸው አይኖች ይዞ ተወለደ። እንደተፈራውም አድጎ አባቱን በመተካት አጼ ለመባል በቃ።

(ዘሪሁን አስፋው፣ 1996፣ ገጽ 33)

**ተግባር**

በአካባቢያችሁ ከሚነገሩ አፈ ታሪኮች አንዱን ጠይቃችሁ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

# ምዕራፍ አስር

## አጭር ልቦለድ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፦

- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጣችሁ ትለማመዳላችሁ፤
- በራሳችሁ ፍጥነት አጫጭር ልቦለዶችን ታነብባላችሁ፤
- የልቦለድ አላባውያንን (ገጸ ባህርያትንና መቼትን) ትለያላችሁ።

## ሀ ማዳመጥና መናገር

### ትምህርት አንድ ፡- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጦ መለየት

**ማስታወሻ**

የንግግር ድምጸት ማለት አንድ ተናጋሪ ሀሳቡን በንግግር ሲገልጽ የተጠቀመውን የድምጽ ቃና ወይም የድምጽ ከፍታና ዝቅታ በማጤን የተናገረበትን ስሜት እና የንግግሩን መንፈስ የምንረዳበት ነው፡፡ እነዚህ የንግግር ድምጸቶች አንዳንዶቹ በጽሑፍ ውስጥ በሥርዓተ ነጥቦች ይገለጻሉ፡፡ ለምሳሌ በሚከተሉት የንግግር ዐውዶች የሚታዩትን የንግግር ድምጸቶች መምህራችሁ ሲያስደምጧችሁ እናንተ ለመለየት ሞክሩ፡፡

**ዐውድ አንድ**

በትህትና ብድር የሚጠይቅ ሰው

ምሳሌ፡-

ባንጃ፡- ቤቶች! ሰው የለም እንዴ?ደህና አደራችሁ?

ሞሊቴ፡- ማነው?ውይ ባንጃ ነህ እንዴ? ደህና አደርክ ና ግባ፡፡

ባንጃ፡- ደህና ነኝ ይመስገነው፡፡

ሞሊቴ፡- ግባ ግባ

ባንጃ፡- አይ አልገባም፡፡ እንደው የሆነ ነገር ቸግሮኝ ነበር የመጣሁት፡፡

ሞሊቴ፡- ምነው ምን ሆንክ?

ባንጃ፡- ትንሽ ገንዘብ ቸግሮኝ ነበር እባክሽ፡፡ እንደው ላስቸግርሽ ከሁለት ቀን በኋላ የምመልሰው 200 ብር ብትፈልጊልኝ፡፡

ሞሊቴ፡- ውይ በሞትኩት! አሁኑኑ እሰጥሀለሁ፤ቆይ እዚሁ ጠብቀኝ፡፡

ባንጃ ፡- በእውነት በጣም ጨንቆኝ ነበር፡፡ ፈጣሪ ይስጥሽ አመሰግናለሁ፡፡

**አውድ ሁለት**

በቁጣ ስሜት ውስጥ ሆኖ የሚናገር ሰው

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| አልቶ፡- | ልጆች! ማነህ ጊዴ ማነው ይህንን ጠርሙስ የሰበረው?! |
| ጊዴ፡- | ውይ! ተሰበረ እንዴ? እኔ አላየሁም አባ፤ ማሚቴ ትሆናለች ቅድም ስትነካካ ነበር፡፡ |
| አልቶ፡- | ማሚቴ! ነይ እስቲ ወዲህ! ለምንድን ነው ጠርሙሱን የሰበርሽው? |
| ማሚቴ፡- | አውቄ አይደለም አባ ይቅርታ፡፡ ዕቃ ስፈልግ ድንገት ወድቆ ተሰበረብኝ፡፡ |
| አልቶ፡- | አትጠነቀቂም! የመድሀኒት ማስቀመጫ ጠርሙስ ነበር፡፡ በይ አሁን ሌላ ጠርሙስ ፈልጊልኝ፡፡ |
| ማሚቴ፡- | እሺ እፈልጋለሁ፡፡ |

**ዐውድ ሦስት**

ታሞ የተኛ ሰው ጠያቂን ሲያናግር

**ምሳሌ፡-**

| | |
|---|---|
| አይሻ፡- | ቤቶች! እንደምን አደራችሁ? |
| ደምሴ፡- | ደህና አደርሽ አይሻ? ግቢ፡፡ |
| አይሻ፡- | ደህና አላህምዱሊላሂ እንዴት ነህ ተሻለህ? |
| ደምሴ፡- | እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ምንም አልልም፡፡ |
| አይሻ፡- | ዛሬ ፊትህም ጥሩ ነው የተሻለህ ይመስላል፡፡ |
| ደምሴ፡- | አዎን ይመስገነው በጣም ለውጥ አለኝ፡፡ |
| አይሻ፡- | እንደው አቅምህን ቢጠግንልህ ብዬ ትንሽ ምግብ አምጥቼልሀለሁ፡፡ ትንሽ ቅመስ፡፡ |
| ደምሴ፡- | ለምን ተቸገርሽ? ምግብ አላስበላ ብሎኝ ከነጋ ምንም አልቀመስኩም፡፡ እንግዲህ ካመጣሽ አይቀር ትንሽ ቀንሰሽ ስጪኝ፡፡ |

## መልመጃ

የሚከተለውን በሁለት የታገቱ ሰዎች መካከል የተደረገ ምልልስ ጥንድ እየሆናችሁ በየተራ ድምጻችሁን በማሰማት እያነበባችሁ የጥያቄና የመገረም ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች ለዩ፡፡

## ታጋቾቹ

“የት ነው ያለነው?”

“ምን ማለት ነው የት ነው ያለነው ማለት?” አለ አንደኛው ታጋች የበኩሉን ግር እያለው፡፡

“የት ነው ያለነው?” አለ ሁለተኛው ታጋች ጥያቄውን አጠናክሮ ደገመው፡፡

“እንዴ!...ሆቴል ነዋ!”

“ማን የሚባል ሆቴል?”

“እኔ እንጃ፣ ስሙን እንኳን አላየሁትም፡፡” አለ የበለጠ እየተነቃቃ፡፡

“ቆይ እሺ የት ሰፈር ነው?”

“እኔም አላወኩትም፡፡”

“አላወኩትም? ይህን ይወዳል ሰውዬው!” ወደመስኮቱ ሄደና ውጪውን አየት አድርጎ እንደገና ወደሱ በመዞር “እኔ ምልህ እኔና አንተ እዚሁ ነው የተገናኘነው?”

“እንዴ! ምን ሆነሃል? ምንም አታስታውስም? እነሱ ናቸው እንጂ ያመጡን፡፡”

“ከየት ነው ያመጡን?”

“ወይኔ ጉዴ.......! ”ግራ በመጋባት እያስተዋለው “ግን ከምርህ ነው?”

“አዎ- ትዝ አይለኝም፡፡”

## ለ ማንበብ

### ትምህርት ሁለት፡- አጫጭር ልቦለዶችን ማንበብ

#### ተግባር

ቀጣዩን ጥያቄ በቃል መልሱ፡፡

1. አጭር ልቦለድ ምንድን ነው?

**ማስታወሻ**

ልቦለድ ደራሲው በእውነተኛው አለም ከተመለከታቸው ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች በመነሳት የራሱን ፈጠራ በማከል የሚያቀርበው ጽሑፍ ነው፡፡ የልቦለድ ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ ይባላሉ፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ አጭር ልቦለድን ትመለከታላችሁ፡፡

አጭር ልቦለድ፡- በጥድፊያ የተሞላ፣ ቁጥብ የሆነና አንድን ነጠላ ጉዳይ ብቻ ይዞ የሚጻፍ የልቦለድ ዓይነት ነው፡፡

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያስደምጧችሁን አጫጭር ልቦለዶች አዳምጡ፡፡ ቀጥሎም መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት በራሳችሁ ፍጥነት በቤታችሁ አጫጭር ልቦለዶችን አንብባችሁ ታሪኩን በአጭሩ ጽፋችሁ በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ትምህርት ሦስት፡- የልቦለድ አላባውያንን መለየት

**ማስታወሻ**

**የልቦለድ አላባውያን/ፍሬ ነገሮች**

የልቦለድ አላባውያን በአንድ ልቦለድ ውስጥ እርስ በእርስ ተሳስረው የሚገኙ የልቦለዱ መሰረታዊ አካል ናቸው፡፡ የልቦለድ አላባውያን ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ መቼት፣ ግጭት፣ ጭብጥና አንፃር ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ስለ ገጸ ባህርያትና መቼት ትማራላችሁ፡፡

**ገጸ ባህርያት፡-**

ገጸ ባህርያት በልቦለድ ታሪክ ውስጥ ሰዋዊ ባህርያትን ተላብሰው እንደሰው ሲያዝኑ ሲደሰቱ፣ ሲበሉ ሲጠጡ ወይም ሌሎችንም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ድርጊቶችና ባህሪያት የሚያሳዩ ደራሲው በምናብ የፈጠራቸው የልቦለድ ዓለም ሰዎች (ባለታሪኮች) ናቸው፡፡ የልቦለድ ገጸ ባህርያት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ዋና ገጸ ባህርያትና ንዑስ ገጸ ባህርያት ናቸው፡፡ ዋና ገጸ ባህርያት ከልቦለዱ መነሻ እስከማብቂያው ድረስ በዘላቂነት የሚገኙና ታሪኩ በዋነኛነት በእነሱ ዙሪያ የሚቀርብ ሲሆን ንዑስ ገጸ ባህርያት ደግሞ ዋና ገጸ ባህርያትን ለማጉላት የሚመጡና በታሪኩ ውስጥ እየታዩ የሚጠፉ ናቸው፡፡

**መቼት፡-**

በልቦለድ ውስጥ **መቼ** እና **የት** የሚሉ ቃላትን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ **መቼ** የሚለው ቃል በልቦለዱ ውስጥ የቀረበው ታሪክ የቀረበበትን ጊዜ የሚወክል ሲሆን የት የሚለው ቃል ደግሞ እንደጊዜው ሁሉ የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበትን ቦታ የሚመለከት ነው፡፡

## ተግባር

ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ልቦለድ አንብባችሁ ከልቦለዱ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

### የጉለሌው ሰካራም

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማን ነው ብለው ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች፤ ተበጀ ሰካራሙ ተበጀ ዶሮ ነጋዴው፤ ተበጀ ነው ብለው ይነግሯቸዋል፡፡

የሕይወቱ ታሪክ ፍፁም ገድል ነው፡፡ ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው፡፡ ጸጉሩ ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም፡፡ ማለዳ አይናገርም፡፡ በጠርሙስ የከመረውን ከጠጣ በኋላ ሲራገም ወይም ሲሳደብ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምፅ ይወፍራል፡፡ ቢያውቀውም ባያውቀውም ላገኘው ሁሉ ማታ ሰላምታ ይሰጣል፡፡ ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ሁሉ ጋር ማታ ይስቃል፡፡ ቢያውቀውም ባያውቀውም የሰላምታው አይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው፡፡ ከሰላምታው ጋር ድምፅ ትሰማለችሁ፡፡ ከአፉ ከሚወጣው ግን አንድ ቃል መለየት አትችሉም፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር የሰካራም ተረት የተጫወተ ሰው ሁሉ የሚናገረው በተበጀ ላይ ነው፡፡ መልኩን አይተውት ያላወቁት ባልቴቶች እንኳ ፍንጃል ቡና ፋት እያሉ የሌላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ ያላክኩት ነበር፡፡

ከዱሮ የእንጨት ጉሙሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ከፍ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት

የተበጀ ቤት ነው፡፡ እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሰራው እርሱ ነው፡፡ ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል፡፡

ቤቱን ሲያይ ተበጀን ኩራት ተሰማው፡፡ ቆይቶ ደግሞ አይኖቹ እንባ አዘሉ፡፡ በጉንጬም የእንባ ዘለላ ወረደው፡፡ በግራ እጁ መዳፍ ከጉንጩ የተንከባለለውን እንባ ጨፈለቀው፡፡ ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱት ለራሱ ጎጆ ስላለው ነው፡፡ ሊነገር በማይችል ደስታ ልቡ ተላውሷል፡፡

ዝናም ያባረራቸውም ከቤቱ ጥግ ሊጠለሉ ይችላሉ፡፡ ቤት የእግዚአብሄር ነውና ውሽንፍር እንዳያገኛቸው ከቤት ውስጥ ዝናቡ እስኪያባራ ይቆያሉ፡፡ ተበጀን “ቤትህን ይባርክ” ሊሉት ነው፡፡

እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ “ይህ የማን ቤት ነው ?” ብሎ ሲጠይቅ “የተበጀ ነው” ሊባል ነው ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ “ተበጀ የትኛው ነው”? ሲባል ዶሮ ነጋዴው ሊባል ነው” አለ፡፡

“ዶሮ ነጋዴው የትኛው ነው” ሲባል “ያ የጉለሌው ሰካራም” ሊባል ነው፡፡ አወይ፤ እኔ ተበጀ፤ ተበላሸቻለሁ አለና ደነገጠ፡፡ ከዚህ በኋላ ስለቤቱ ክብር እንኳ መጠጥ መተው ይገባኛል አለ ፡፡

መጠጥ ለመተው ያሰበበት የመጀመሪያ ጊዜው ይህ ነው፡፡ ሰካራምነት ጉዳት መሆኑ ተሰምቶት እንደሆን ይናገር እንጂ ስለ ቤት ክብር ማለቱ ግን ወደ ዳር ይቆይ፡፡ ስለ ቤት ክብር ምን ያውቃል? ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ሰካራሙ ተበጀ አይደለምን ?

ሰካራሙ ተበጀ የሰራውን የገዛ ቤቱን ከፍቶ ገባና ኩራዙን አስቀምጦ ክብሪቱን ለመጫር ሲያወጣ በሐሳብ ተሰቅዞ እንደዚህ አሰበ፡፡ መምረጥ አለብኝ፡፡ ከዚህ ቤት

ያለው መጠጥ ሁሉ አንድ ሳይቀር እየወጣ ይፍሰስ። ከዚህ በኋላ ክብሪቱም ኩራዙም በቤት ይደር፤ በአዲሱም ቤት ብርሃን ይዙርበት። ሊደረግ የሚገባው ከሁለቱ አንዱ ነው እንጂ በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳት በአንድነት! የማይሆን ነገር ነው።

ከሁለቱ አንዱን ለማድረግ ሳይቆርጥ መብራቱን አቃጠለና ተቀመጠ። እንደገና ደግሞ እንደዚህ አሰበ። አያድርገውና ዛሬ ሰክሬ ይህ ቤት ቢቃጠልብኝ አመዱን አይቶ በሰካራሙ ተበጀ ላይ ለመሳቅ ድፍን ጉለሌ ነገ ከዚህ ነው የሚቆም! ጉለሌ ምን ባለኝ? ወሬ ከማበካት በቀር ጉለሌ ምን ሥራ አለው? ለአዲስ አበባም የስድስት ወር መሳቂያ በሆንኩ ነበር። መንገድ አላፊዎችም ነገ በዚህ ሲያልፉ አመዱን አይተው ይህ “የተቃጠለው ቤት የማን ነበር” ሲሉ የተበጀ ሊባል ነው።

ወደ ውጭ እንደ እርም ወርውሮት የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ ሁሉ በጨለማው ዳብሶ አንድ በአንድ ለቃቀማቸው። አንዱን ግን ቀና አደረገና ከአፍንጫው አስጠግቶ አሸተተው። በጠርሙሱ ቅርፅ የመጠጡን አይነት አወቀው። አረቄ ነበርና ሰው እንዳይሰማ ቀስ ብሎ ሳቀ።

“ጉለሌ ተኝቷልና ከዚሁ ከባሕር ዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ብጠጣ የሚታዘበኝ የለም” አለና አሰበ። እውነቱን ነው። ጉለሌስ ተኝቶ ነበር ነገር ግን አሁን እርሱ ጠጥቶ የሰከረ እንደሆነ ጉለሌን ሊቀሰቅሰው ነው እርሱ ከጠጣ በጉለሌ ማን ይተኛል?

ጠርሙሱን ከከፈተው በኋላ ብርጭቆ ያስፈልገው እንደነበር ትዝ አለው። ሶስት የሚሆን ደህና ጉንጭ ጠርሙሱን ከአፉ አስጠግቶ ጨለጠ። ከዚያ በኋላ የሚጠጣበት ብርጭቆ ሊያመጣ አሰበ። በሶስት ጉንጭ ምን ያህል እንደጠጣ ጠርሙሱን ቀና አድርጎ በጨረቃዋ ተመለከተ። “ግማሹን ያህል ሰርጉጄዋለሁ” አለና በሳቅ ፈነዳ። “ለዚህችስ ብርጭቆ ማምጣት አያሻም” እያለ ጠርሙሱን

አምቦጫቦጨው፡፡ በቀኝ ክንዱ መሬቱን ተመርኩዞ የቀረውን ጅው አድርጎ ወደ ውስጥ ወረወረው፡፡

የጠርሙሱ መጠጥ ሁሉ እስኪያልቅ ድረስ ከዚያ ከዛፉ ሥር ተቀምጦ ያን ጠንካራ ትምባሆውን ከአፉ አለየውም፡፡ በሳቅ ጊዜ ብቻ መልሶ ዝም እስኪል ድረስ መጠጡን ወይም ትምባሆውን ከአፉ ያቋርጣል፡፡ የመጠጥና የትምባሆ ጊዜው ተበጀ ይህ ነው፡፡ ማለዳ በቀዝቃዛ ውሃ ታጠበ፡፡ እንቁላል ጠበሰና በዳቦ በላ፡፡

ደክሞት ነበርና ደኅና እንቅልፍ ተኝቶ አደረ፡፡ ዝናቡን፣ ነጎድጓዱን፣ ጎርፉን፣ ውሃ ሙላቱን አልሰማም፡፡ አንዳች ነገር ሰማ፡፡ ዘፈን እና እልልታ የሰማ መሰለው፡፡ ትናንት ከጠጣው መጠጥ ኃይል መሰለውና ይህስ ዕብደት ነው እንጂ ስካር አይደለም አለና ተመልሶ ተኛ፡፡

እንደገና አዳመጠ፡፡ የእርዳታ ጥሪ ጩኸት ሰማ፡፡ ከአልጋው ዘልሎ ከወረደ በኋላ ቤቱን ለመዝጋት ጊዜ አላገኝም፡፡ በትልቁ ወንዝ ዙሪያ ቆመው ይጮሁ የነበሩ ሰዎች የውሃው ሙላት የሰፈሩ ልጅ ስንዱን እንደጠለፋት ነገሩት፡፡ ጎርፍ የወሰደው ልጅቱን ይሁን ወይም ሌላ ለተበጀ ምኑም አይደለም፡፡

"ስንዱን እናንተ በመጨረሻ ያያችኋት ወዴት ነው?" ብሎ ጠየቀና እየጠለቀ በዋና ይፈልግ ጀመር፡፡ ለስንዱ በውሃ ሙላት አንሰዋም ያለው ጉለሌ በዳር ተሰልፎ ቁሞ ተበጀን ይመለከት ነበር፡፡ ብዙ ጠልቆ ከቆየ በኋላ ብቅ አለና "አገኘኋት መሰለኝ "ብሎ በዳር ላሉት ጮሆ ተናገረ፡፡ ለሰው ሁሉ ደስታ ሰጠው፡፡ ከሁሉም ይልቅ እርሱን ደስ አለው፡፡ የጠለቀውና የዋኘው ረጅም ጊዜ ስለሆነ ደክሞት ነበር፡፡ ነገር ግን ሊያወጣት ይገባዋል፡፡ ጠለቀና አገኛት፡፡ በአሽካከሙ ላይ ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ አለዚያስ የውሃው ሙላት እንደገና ይነጥቀዋል፡፡ እንደተሸከማት ውስጥ ለውስጥ ዋኘና ከዳር ብቅ አለ፡፡

ከሽክሙ ክብደት ኃይል የተነሣ ወዲያው ወደቀ። እርዳታ ተነባበሩለትና ጎትተው እርሱንም እርሷንም አወጧቸው።

ተበጀ ተዘርግቶ እያቃተተ የጉለሌ ሰው በሳቅ ሲፈነዳ ሰማ- ከራሱ በኩል ቀና አለና "ሴትዮዋ ድናለች?" ብሎ በርጎራሄ ድምፅ ጠየቃቸው። አንዱ ቀረበና "አሳማ ነው ያወጣኸው" አለው።

የሚያቃትተው ተበጀ ከወደራሱ ቀና አለና "አሳማ?" ብሎ ጠየቀው። "ለመሆኑ ከእናንተ ውሃ የወሰደባችሁ ሰው ነበር ወይስ አሳማ?" ብሎ ተበጀ ጠየቀና ያቃትት ጀመር።

ጎረቤትህን እንደነፍስህ ውደድ ቢባልም ሰዎችን እንጂ የሰዎችን አሳማዎች አልነበረም። የውሃ ሙላት ነጥቆ ወስዶ የነበረው የጎረቤቱን አሳማ ሳለ ያላዩትን ቢያወሩ ግድ የሌላቸው ሰዎች ስንዱን ውሃ ወሰዳት ብለው አውርተው የተበጀን ነፍስ ለአንድ አሳማ ነፍስ ሊያስለውጡት ነበር። መልካሙ ሥራው ሁሉ ደግሞ እንዲሁ ርካሽ ሆኖ የሚቆጠር የሆነበት ምክንያት ዘወትር የሚሰክር ሆኖ ስለታወቀ ነው።

(ተመስገን ገብሬ በ1941። ገጽ 1-9 ለማስተማር እንዲመች ሆኖ የቀረበ)

## ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በአነበባችሁት የአጭር ልቦለድ መሰረት መልሱ።

   ሀ. የልቦለዱ ባለታሪክ (ገጸ ባህርይ) ማነው?

   ለ. ከዋናው ባለታሪክ (ገጸ ባህርይ) በተጨማሪ በታሪኩ የተገለጹ ሌሎች ባለታሪኮች አሉ? ካሉ ጥቀሷቸው።

ሐ. ዋናው ባለታሪክ (ገጸ ባህርይ) ምን ዓይነት ሰው ነው?

መ. የልቦለዱ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜና ቦታ ግለጹ።

2. መምህራችሁ በሚያስደምጧችሁ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ ባለታሪኮቹን (ገጸ ባህርያቱን) እና መቼቱን ለይታችሁ ተናገሩ።

# ማጣቀሻ ጽሑፎች


በድሉ ዋቅጅራ። 1996። ፍካት ናፋቂዎች የግጥም መድብል። አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት

ባይለየኝ ጣሰው። 1995። የአኝዋ ተረቶች ። ለተማሪዎቹ እንዲስማማ ተደርጎ ተሸሽሎ የቀረበ። አዲስ አበባ።

ተመስገን ገብሬ። 1941። የጉለሌው ሰካራም። አዲስ አበባ፣ነጻነት ማተሚያ ቤት።

አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ/የተ/የግ/ማ። 2004። አዲስ አድማስ/ ሳምንታዊ ጋዜጣ/። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ዘሪሁን አስፋው። 1996። የሥነ ጽሑፍ መሰረታዊያን።

የኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት። አዲስ ዘመን/ዕለታዊ ጋዜጣ። አዲስ አበባ ብርሐንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስተር። 2009። አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የ7ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ ።

ዳንኤል ክብረት። 2003። የሁለት ሀውልቶች ወግ። አግዮስ ህትመት። አዲስ አበባ።

ገብረ ክርስቶስ ደስታ። 1998። መንገድ ስጡኝ ሰፊ። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስትትዩት።

ጥላሁን ጣሰው። 2007። የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂና ኑሮ።

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ